ማውጫ

ክፍል አንድ **ገጽ**

1. መግቢያ 3

2. የኤጀንሲው ራዕይ እና አላማ 4
3. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር 4
4. የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅር 5
5. የሥራ ፍሰት መግለጫ /System Description/ 5
6. የኤጀንሲው የሰው ኃይል 6
7. የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ 6
8. የኦዲቱ አላማ 7
9. የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች 7
10. የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ 7
11. የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ /ሥልት/ 8

ክፍል ሁለት

የኦዲቱ ግኝቶች 9

- በጋራ ልማት እና በኪራይ የሚሳተፉ ባለሃብቶች የሚያቀርቡት የሥራ እቅድ ተፈጻሚነትን በተመለከተ 9
- በኤጀንሲው እና የልማት ድርጅቶችን በሚከራዩ እና በጋራ ልማት በሚሳተፉ ባለሃብቶች መካከል በኮንትራት ውሉ ላይ የሚጠበቀው ተግባርና ሀላፊነት በግልጽ እና በፅሁፍ ተሟልቶ መቀመጡን በተመለከተ 10
- በኪራይ ለተያዙ የልማት ድርጅቶች በውል ስምምነቱ ውስጥ የስጋት መጠቆሚያ መስፈርቶች (Periodic Risk Assessment) መኖራቸውን በተመለከተ 10
- በጋራ ልማት እና በኪራይ የሚተዳደሩ ድርጅቶችን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እና የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች መሰራታቸውን በተመለከተ 11
- በጋራ ልማትና በኪራይ የተያዙ ድርጅቶች በስራ እቅዳቸው (Business Plan) መሠረት ለመፈጸማቸው የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ 12
- በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች የቦርድ ጽ/ቤት በየሶስት (3) ወሩ ስለስራ ሂደቱ ለኤጀንሲው ሪፖርት ማቅረቡን በተመለከተ 15
- በጋራ ልማት እና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሂሳብ መግለጫዎች (ሪፖርቶች) በወቅቱ መዘጋጀታቸውንና ኦዲት መደረጋቸውን በተመለከተ 16
- በኪራይ ከተያዙ የልማት ድርጅቶች የሚፈለግ ያልተከፈለ የኪራይ እዳ እና ሌሎች

የመንግስት እዳዎችን እንዲሁም ውል ቢቋረጥ አፈጻጸሙ በስምምነት ሰነዱ መሰረት መሆኑን በተመለከተ 16
- በጋራ ልማት እና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች የትርፍ ድርሻ (dividend) እና የኪራይ ክፍያን በተመለከተ 19
- የልማት ድርጅቶች በኪራይና በጋራ ልማት ከተያዙ በኋላ ያስከተሉት አጠቃላይ ውጤት ኤጀንሲው በተወሰነ የጊዜ ገደብ መገምገሙን በተመለከተ 21
- በጋራ ልማትና በኪራይ በተያዙ የልማት ድርጅቶች ስር ያሉ የኤጀንሲው ንብረቶች አያያዝን በተመለከተ 21
- በኪራይና በጋራ ልማት እየለሙ የሚገኙ ድርጅቶች ውስጥ ያለ የባለሃብት እና ሰራተኛን ግንኙነት በተመለከተ 23
- በጋራ ልማት እና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች ዙሪያ በኤጀንሲው ያለውን የመረጃ ሥርዓት በተመለከተ 25

ክፍል ሦስት

- መደምደሚያዎች 26

ክፍል አራት

- የማሻሻያ ሃሳቦች 28

አባሪዎች

- አባሪ 1 ድርጅታዊ መዋቅር 30
- አባሪ 2 የአሰራር ሥርዓት መግለጫ 31
- አባሪ 3 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች 33

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. የአገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት ለማፋጠንና የልማት ድርጅቶች በመንግስት ይዞታ ሥር እስካሉ ድረስ ተወዳዳሪና አትራፊ ሆነው በመቀጠል የሃገሪቱን የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ በማስፈፀምና ኢኮኖሚያዊ እድገት በማምጣት ረገድ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ የሚያስችል አመራርና ድጋፍ መስጠት በማስፈለጉ የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣንን በማዋሃድ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 412/1996 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡ በአዋጁ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በስሩ የሚገኙ የልማት ድርጅቶችን በመምራትና በመቆጣጠር ለውጤት ማብቃት፤ ልማት ድርጅቶችን ግልጽ በሆነ መንገድ የተለያዩ የፕራይቬታይዜሽን ስልቶችን በመጠቀም ወደ ግል ባለሃብቶች ማዛወርና በግል ባለሃብቱ የማይሸፈኑና ለአገሪቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ወሳኝ በሆኑ ዘርፎች ደግሞ የገበያ ክፍተቶችን መሙላት የሚችሉ ፕሮጀክቶችን ማጥናትና ልማት ድርጅቶች እንዲቋቋሙ ማድረግ ቁልፍ ተግባሮቹ ናቸው፡፡
2. የፕራይቬታይዜሽን ስርዓቱን ለማጠናከርና አፈጻጸሙን ለማፋጠን መንግስት በእጁ የሚገኙ የልማት ድርጅቶችን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በሽያጭም ሆነ በሌሎች ፕራይቬታይዜሽን ስልቶች ወደ ግል ባለሃብቶች ለማዛወር ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል፡፡በዚህም እንቅስቃሴ ከ1987-1997 ዓ.ም ድረስ ባሉት አስር ዓመታት 213 ድርጅቶችና ቅርንጫፎች ወደ ግል በማዛወር ብር 3.13 ቢሊዮን ገቢ ተገኝቷል፡፡ ከ1998-2003 ዓ.ም ባሉት ስድስት ዓመታት ደግሞ 97 ድርጅቶችና ቅርንጫፎች በብር 5.6 ቢሊዮን ወደ ግል ተዛውረዋል፡፡ በድምሩ ባለፉት አስራ ስድስት ዓመታት 310 የልማት ድርጅቶችና ቅርንጫፎች በጨረታ ሽያጭና በሌሎች ዘዴዎች ወደ ግል ተዛውረው ብር 8.7 ቢሊዮን ገቢ ተገኝቷል፡፡
3. በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ የመንግስት የሆኑ የልማት ድርጅቶች ብዛት 67 ሲሆኑ የተወሰኑ አክሲዮኖች በመያዝ ከግል ባለሃብቶች ጋር በጋራ ልማት የሚያስተዳድራቸው 11 ድርጅቶች፣ በኪራይ ለተወሰነ ጊዜ (በሊዝ) ወደ ግል ባለሃብት የተዛወሩ 7 ድርጅቶች እንዲሁም የገበያ ክፍተቶችን በመሙላት ለእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሳካት የጎላ አስተዋፅኦ ያላቸውና በተለያዩ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ የሚገኙ 3 አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በመምራትና በማስተዳደር ላይ ይገኛል፡፡ ባለስልጣን መ/ቤቱ በከለሰው የአምስት ዓመት (2003-2007 ዓ.ም) የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም መሰረት 22 የልማት ድርጅቶች በቀጣዩ አምስት ዓመት በመንግስት እጅ የሚቆዩ ሲሆን ቀሪዎቹ 62 የልማት ድርጅቶች (በሊዝ የተያዙና በመንግስት የተያዙ አክሲዮኖችን ጨምሮ) የተለያዩ የፕራይቬታይዜሽን ስልቶችን በመጠቀም ወደ ግል ባለሃብቶች እንዲዛወሩ ይደረጋል፡፡

የኤጀንሲው ራዕይ እና ዓላማ

ራዕይ

4. "ብቁና ተወዳዳሪ የሆኑ የልማት ድርጅቶች ተፈጥረው ግልፅና ቀልጣፋ በሆነ አሰራር ወደ ግል ተዛውረው ማየት"

አላማ

5. ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-
   - ✓ የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር ግልፅና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ እንዲፈጸም ማድረግ፣
   - ✓ የመንግስት የልማት ድርጅቶች አቅማቸውን በተሻለ ደረጃ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ በማስቻልና የተሻሻሉ የማኔጅመንት ሥርዓቶችንና ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሥራ አፈፃፀማቸው እንዲሻሻልና የላቀ ውጤት እንዲያመጡ ማገዝ፣
   - ✓ በተለያዩ ምክንያቶች የግል ባለሃብቶች ሊሳተፉ ባልቻሉ ለኢኮኖሚው አጠቃላይ ልማት ማነቆ ሊሆኑ በሚችሉ ዘርፎች አዳዲስ የልማት ድርጅቶች እንዲቋቋሙ ማድረግ፣
   - ✓ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን አመራር መቆጣጠር እና
   - ✓ በመንግስት የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማኅበራት የመንግስትን የባለቤትነት መብት ማስከበር፣

የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

6. ለኤጀንሲው በአዋጅ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት በሁለት ዋና ዋና ፈርጆች የሚከፈሉ ናቸው፡፡ እነዚህም የፕራይቬታይዜሽንን ፕሮግራም ማስፈፀምና የልማት ድርጅቶችን መምራት ናቸው፡፡

   6.1. የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራምን የተመለከቱ አበይት ተግባራት፡-
   - ✓ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶች እንዲከናወኑ ማድረግ፤
   - ✓ በፕራይቬታይዜሽን የሚተላለፉ ባለሃብቶች የሚወዳደሩባቸውን መመዘኛዎች መወሰንና፣ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች ተሳትፎ ሊበረታታ የሚችልበትን መንገድ መቀየስ፣
   - ✓ ከመንግስት ጋር በቅንጅት ኢንቨስት ለማድረግ የሚፈልጉ ባለሃብቶች የሚያቀርቧቸውን የፕሮጀክት ሃሳቦች መገምገምና ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አቅርቦ ማጸደቅ፣ ተግባራዊነታቸውንም መከታተል፤
   - ✓ የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራምና አፈጻጸሙ በህዝብ እንዲታወቅ ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ፤

- ✓ የድህረ ፕራይቬታይዜሽን ክትትል በማድረግ በፕራይቬታይዜሽን የተሳተፉ ባለሃብቶች የገቧቸውን ግዴታዎች ማክበራቸውን ማረጋገጥ፣ ፕራይቬታይዜሽን ካስከተለውን አጠቃላይ ውጤት መገምገም፡፡

6.2. **የመንግስት ልማት ድርጅቶች መምራትን የሚመለከቱ ተግባራት፡-**

- ✓ በተለያዩ ምክንያቶች የግል ባለሃብቶች ሊሳተፉ ባልቻሉባቸው መስኮች የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም የፕሮጀክት ጥናቶችን ማካሄድ፤
- ✓ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን አቅም ለመገንባት የሚረዱ ጥናቶችን በማካሄድ አጠቃላይ መመሪያዎችን መስጠት፤
- ✓ የልማት ድርጅቶችንና ሙሉ በሙሉ በመንግስት የተያዙ አክስዮን ማህበራትን የሚያስተዳድሩ የቦርድ ሰብሳቢና አባላትን መመደብ፣ ማንሳት እና አበላቸውን መወሰን፤
- ✓ የልማት ድርጅቶችን አጠቃላይ ግቦችና የኢንቨስትመንት እቅዶችን ማጽደቅ፣ አፈጻጸማቸውንም መከታተልና መገምገም እንዲሁም ለቦርድና ማኔጅመንት አባላት ተፈጻሚ የሚሆን በውጤት ላይ የተመሰረተ የማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋትና ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፤
- ✓ የልማት ድርጅቶችን የውጭ ኦዲተሮች ምደባ እና የተመረመሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ማጽደቅ ናቸው፡፡

የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅር

7. የፕራይቬታይዜሽንና መንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ተጠሪነቱ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ለፕራይቬታይዜሽን ቦርድ ሲሆን፣ ኤጀንሲው በአንድ ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ነው፡፡ በዳይሬክተሩ ስር የኦፐሬሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና የፕራይቬታይዜሽንና የፕሮጀክት ጥናት ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ይገኛሉ፡፡ በኦፐሬሽን ዘርፍ ሥር የኮርፖሬት አመራር እና የኮርፖሬት አቅም ግንባታና ድጋፍ ዳይሬክቶሬቶች ሲገኙ፣ በስራቸውም የዕቅድና መረጃ ሥራ አመራር፣ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን እና የኦዲት ዳይሬክቶሬት ይገኛሉ፡፡ በፕራይቬታይዜሽንና የፕሮጀክት ጥናት ዘርፍ ስር ደግሞ የፕሮጀክት ጥናትና ትግበራ እና የፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት ሲገኙ፣ በስራቸው የአሰራር ማሻሻያና የሰው ሃብት፣ የህግ እና የፋይናንስና አቅርቦት ዳይሬክቶሬት ይገኛሉ፡፡ ዝርዝሩ <u>በአባሪ-1</u> ተያይዟል፡፡

በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት የተያዙ የልማት ድርጅቶችን የሚመለከቱ የሥራ ሂደቶች የሥራ ፍሰት (System Description) መግለጫ

<u>**የፕራይቬታይዜሽን ዝግጅትና አፈጻጸም የሥራ ፍሰት**</u>

8. በፕራይቬታይዜሽን ዝግጅትና አፈፃፀም የስራ ሂደት ስር የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ይከናወናሉ፡-

- ✓ ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር እንዲቻል ጥናቶችን ማድረግና ለዋጋ ትመና የሚያስፈልጉ መረጃዎች ወቅታዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ✓ የንብረት ዋጋ ትመና ማዘጋጀት እና የጨረታ ሰነድ ማዘጋጀት፣
- ✓ ከባለሃብቶች የሚቀርቡ የስራ ዕቅዶችን (Business plan) መገምገም፤ ማፅደቅ እና ከባለሃብት ጋር ድርድር ማድረግ፣
- ✓ የውል ስምምነቶችን ማዘጋጀትና ስምምነት የተደረሰባቸውን ድርጅቶች ማስረከብ ናቸው።

<u>የድህረ ፕራይቬታይዜሽን ክትትልና ድጋፍ የሥራ ፍሰት</u>

9. በድህረ ፕራይቬታይዜሽን ክትትልና ድጋፍ የሥራ ፍሰት ስር የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ይከናወናሉ፡-
   - ✓ ወደ ግል ይዞታ በተዛወሩ ድርጅቶች ባለሃብቶች በገቡት የውል ግዴታ መሰረት መፈፀማቸውን መከታተል፣
   - ✓ የተሸጡ ድርጅቶች ያጋጠማቸውን ችግሮች በመለየት ድጋፍ መስጠት
   - ✓ ወደ ግል ይዞታ ከተዛወሩ ድርጅቶች መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተንና ሪፖርት ማቅረብ ናቸው።

የፕራይቬታይዜሽን ዝግጅትና አፈጻጸም እና የድህረ ፕራይቬታይዜሽን ክትትልና ድጋፍ የሥራ ፍሰት ስዕላዊ መግለጫ <u>በአባሪ-2</u> ተያይዟል።

የኤጀንሲው የሰው ሃይል

10. ለኤጀንሲው በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል 332 ሲሆን፣ በ2004 የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት 208 የሰው ኃይል በሥራ ላይ ይገኛል። ከዚህም ውስጥ የሴት ብዛት 90 (43%) እና የወንድ ብዛት 118 (57%) ነው። አሁን ያለው የሰው ኃይል በሙያ ሲተነተን የኘሮፌሽናል የሰው ሃይል ብዛት 107 (51%)፣ መለስተኛ ኘሮፌሽናል ብዛት 7 (3.4%) እና ከዛ በታች ያሉ ሰራተኞች ብዛት 94 (45%) ናቸው።

የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ

11. የፕመልድተኤ የፋይናንስ ምንጭ ከመንግስት የሚመደብለት በጀት ሲሆን፣ በ2002፤ በ2003 እና በ2004 በጀት ዓመት በቅደም ተከተሉ ብር 6,125,400 /ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ አራት መቶ ብር/፣ ብር 8,925,689.85 /ስምንት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃያ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ብር ከሰማንያ አምስት ሣንቲም/ እና ብር 14,953,700 /አስራ አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ብር/ መደበኛ በጀት የተፈቀደ ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ በ2002 በጀት ዓመት ብር 5,887,965፣ በ2003 በጀት ዓመት ብር 8,466,321.69 እንዲሁም በ2004በጀት ዓመት ብር11,770,526.93 ወጪ ሆኗል።

የኦዲቱ ዓላማ

12. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲው በኪራይና በጋራ ልማት የተያዙ የልማት ድርጅቶች ከሀገሪቱ የልማት ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ እና መሰረታዊ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ እንዲሆኑ እገዛ የሚያደርግ እና የሚከታተል መሆኑን ለመገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮችን ለማቃለል የሚያግዙ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት ነው፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

13. ከላይ የተመለከተውን የኦዲት አላማ ለማሳካት ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) እና አራት ንዑስ የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Sub-Issues) ተነድፈዋል፡፡ እነርሱም፤
    - 13.1. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችን በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት በሚይዝበት ወቅት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች ተሟልተው የሚከናወኑ መሆናቸውንና ቀጣዩ ሥራም ኢኮኖሚያዊና ብቃት ባለው ሁኔታ እንዲፈፀም ለማድረግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋ እና ተግባራዊ መሆኑን መገምገም፣
    - 13.2. የልማት ድርጅቶችን በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ከተያዙ በኋላ ኢኮኖሚያዊና ብቃት ባለው ሁኔታ እንዲከናወኑ ሁኔታዎችን የሚያመቻች፤ ድጋፍና ክትትል የሚያደርግ መሆኑን መገምገም ሲሆን፣ ይህም በአራት ንዑስ የኦዲት ጭብጦች ተከፍሏል፡፡
        - 13.2.1. የመንግስት የልማት ድርጅቶች በኪራይ ወይም በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት በሚዛወሩበት ወቅት የድርጅቱ ነባር ሰራተኞች አያያዝን መገምገም፣
        - 13.2.2. በኪራይ ወይም በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት የተያዙ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ንብረት አጠባበቅና አያያዝ በብቃትና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መልኩ መሆኑን መገምገም፣
        - 13.2.3. በኪራይ ወይም በጋራ ኢንቨስትመንት የተያዙ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሥራ አፈፃፀምና ውጤት በታቀደለት መሰረት መሆኑን መገምገም፣
        - 13.2.4. ኤጀንሲው ከልማት ድርጅቶች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር እንዲሁም በልማት ድርጅቶች መካከል ቅንጅታዊ አሠራር መዘርጋቱንና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን ማረጋገጥ ናቸው፡፡

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria)

14. ለኦዲቱ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ መቋቋሚያ

አዋጅ፣ ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ የተለያዩ መመሪያዎች፣ ድረ-ገፅ እና ቃለ መጠይቆችን መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ለተመረጡት ሁለት የኦዲት ጭብጦች እና አራት ንዑስ የኦዲት ጭብጦች 36 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች የተዘጋጁ ሲሆን፣ መስፈርቶቹም ለሚመለከተው ዳይሬክቶሬት ተልኮ አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 3 ተያይዘዋል፡፡

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ /ስልት/

15. የክዋኔ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2002 ዓ/ም እስከ 2005 ሩብ አመት ሲሆን፣ በዚህ ጊዜ ውስጥ በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት የተያዙ የመንግስት የልማት ድርጅቶች አፈፃፀም ላይ የተከሰቱ አበይት ክፍተቶችን ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2002 ዓ.ም. በተሰጠው ስልጣን መሰረት እና በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች /Ethiopian Performance Audit Standards/ መሰረት ሲሆን፣ ለክዋኔ ኦዲቱ በተዘጋጁ የመመዘኛ መስፈርቶች መሰረት መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነው እና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ሰራተኞች ቃለ-መጠይቅ ተደርጓል፡፡

    ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት ሲሆን፣ ከድህረ ፕራይቬታይዜሽን እና ከአጋር ማፈላለግ የሥራ ቡድኖች ጋር ቃለ-መጠይቅ በማድረግ እና የመረጃ ክለሳ በማድረግ ነው፡፡

    በተጨማሪም በክልል እና በፌደራል የሚገኙ እና በናሙና ከተመረጡ በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት እየለሙ ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች ከአርባ ምንጭ እርሻ ልማት እና መዳመጫ፣ ከሲሌ እርሻ ልማት፣ ከአቢጃታ ሶዳ አሽ አክሲዮን ማህበር፣ ከአምቦ ውሃ አክሲዮን ማህበር፣ ከቢኤም ኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ሃላፊነቱ የተወሰነ ድርጅት እና ከሆራይዘን አዲስ ጎማ አክሲዮን ማህበር፣ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች፣ የንብረት ክፍል፣ የሰራተኛ ተወካዮች እና የቦርድ አባላት ጋር ቃለ-መጠይቅ በማድረግ እና መረጃዎችን በመሰብሰብ እንዲሁም የቀድሞ የአርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ፣ አዋሳ ጨርቃ ጨርቅና የሲሌ እርሻ ልማት ተከራዮችን በተመለከተ መረጃዎችን በመከለስ ተተንትነዋል፡፡

ክፍል ሁለት

የኦዲቱ ግኝቶች

በጋራ ልማት እና በኪራይ የሚሳተፉ ባለሃብቶች የሚያቀርቡት የሥራ እቅድ ተፈጻሚነትን በተመለከተ

16. ኤጀንሲው የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ከግል ባለሃብቶች ጋር በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ለመያዝ የተቀመጠ ግልፅ የመምረጫ እና የማወዳደሪያ መስፈርት ሊኖረው ይገባል፡፡ የመምረጫ መሥፈርቱም ሊተገበርና ስኬታማነቱ ሊረጋገጥ የሚችል መሆን አለበት፡፡
17. ኤጀንሲው የልማት ድርጅትን በጋራ ለማልማት የሚፈልግን ባለሃብት ለመምረጥ በባለሃብቶች የሚቀርበውን የሥራ ዕቅድ እንደ ዋነኛ የመምረጫ መስፈርት በመጠቀም የተሻለውን የሥራ ዕቅድ ያቀረበውን ድርጅት (ባለሃብት) ገምግሞ የሚመርጥ መሆኑ ታውቋል፡፡
18. የኤጀንሲው ሃላፊዎችም ስለአመራረጡ በሰጡት ምላሽ፣ አጋሮች የሚመረጡት የተሻለ የሥራ ዕቅድ ይዘው በመቅረባቸውና በተለይም በዕቅዱ ውስጥ በኢንቨስትመንት፣ በኤክስፖርት፣ በአቅም አጠቃቀም እና በቴክኖሎጂና በአሰራር ስርዓት በአንፃራዊነት ከሌላው የተሻሉ ሆነው ሲገኙ የሚመረጡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም የኤጀንሲው ሃላፊዎች በመጨረሻ ሪፖርት ላይ በሰጡት አስተያየት ባለሃብቶች ያቀረቡትን ዕቅድ ለማስፈጸም የሚያስችል አቅም ያላቸው ስለመሆኑ የተለያዩ መንገዶችን (የሰነድ፣ የገፅ ዕይታና በውጪ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችን በመጠቀም) ለማረጋገጥ እንደሚሞከርና ባለሃብቶቹ የሚያቀርቡት የኪራይ ዋጋ ወይም ለመንግስት መዋጮ የሚሰጡት ዋጋ በመምረጫ መስፈርትነት እንደሚያገለግል ገልፀዋል፡፡
19. ይሁን እንጂ በኦዲቱ በተመለከትናቸውና በዚህ ሪፖርት ውስጥ ችግር የተከሰተባቸው ተብለው ከሚቀርቡት በኪራይና በጋራ ልማት ይዞታ ከተላለፉ አንዳንድ የልማት ድርጅቶች አፈፃፀም እንደተረዳነው፤ ኤጀንሲው ባለሃብቶች የሚያቀርቡትን የሥራ ዕቅድ (Business plan) በተጨባጭ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ወይም የማይችል መሆኑን ለማረጋገጥ የሚጠቀምበት መንገድ በቂ ባለመሆኑ ተፈፃሚ የማይሆኑ ዕቅዶች በባለሀብቶች ቀርበው የተመረጡ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡
20. ስለሆነም የሥራ ዕቅድ በተጨባጭ ተፈጻሚነቱ በበቂ ሁኔታ ሳይረጋገጥ የተሻለ የሥራ እቅድ ያቀረበውን ባለሃብት መምረጥ ትክክለኛውን ባለሀብት ለመምረጥ ካለማስቻሉም በላይ የማይፈፀም የሥራ ዕቅድ እንዲቀርብና ዕቅዱ ተግባራዊ እንዳይደረግ ምክንያት ይሆናል፡፡

በኤጀንሲው እና የልማት ድርጅቶችን በሚከራዩ እና በጋራ ልማት በሚሳተፉ ባለሃብቶች መካከል በኮንትራት ውሉ ላይ የሚጠበቀው ተግባርና ሀላፊነት በግልጽ እና በፅሁፍ ተሟልቶ መቀመጡን በተመለከተ

21.በኤጀንሲው በተከራይ ባለሃብቶች እና በጋራ ልማት በሚሳተፉ ባለሃብቶች መካከል የሚጠበቀው ተግባርና ሀላፊነት በህግ ዘንድ ተቀባይነት ባለው መልኩ በኮንትራት ውሉ ላይ በግልጽ እና በፅሁፍ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

22. ሆኖም በኪራይና በጋራ ልማት ለሚያዙ ድርጅቶች ውል ዝግጅት ላይ የሚታዩ ጉድለቶችና የክፍያ ዘመን የሚጠናቀቅበት ጊዜ ለምሳሌ- በኪራይ ለሚያዙ ድርጅቶች የሚሰጠው የእፎይታ ጊዜ ኪራይ ክፍያ መቼ እንደሚከፈል በግልጽ የማይቀመጥ መሆኑን ከኤጀንሲው የ2002 በጀት አመት የሥራ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

23. ስለሁኔታው የኤጀንሲው ኃላፊዎች በሰጡት መልስ የዕፎይታ ጊዜ ክፍያ በመጀመሪያው አመት ክፍያ ተጠቃሎ እንዲከፈል እየተደረገ እንደሆነ ነገር ግን ይህ ክፍያ በአመቱ ውስጥ በየትኛው ወር እንደሚከፈል በግልፅ እንዳልተቀመጠ ገልፀዋል፡፡

24. በኪራይ ለሚያዙ ድርጅቶች የእፎይታ ጊዜ ኪራይ ክፍያ መቼ እንደሚከፈል በግልፅ አለመቀመጡ ክፍያው ሳይከፈል የሚቀርበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ስለሆነም አሰራሩ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በኪራይ ለተያዙ የልማት ድርጅቶች በውል ስምምነቱ ውስጥ የሥራ ዕቅድን ሊያዘገዩ የሚችሉ የስጋት መጠቆሚያ መስፈርቶች (Periodic Risk Assessment) መኖራቸውን በተመለከተ

25. በኪራይ ለተያዙ የልማት ድርጅት በውል ስምምነት ውስጥ የሥራ ዕቅዱን ሊያዘገዩ ወይም እንዳይፈጸም ሊያደርጉ የሚችሉ ስጋት የሆኑ የስጋት መጠቆሚያ መስፈርቶች (Periodic Risk Assessment) ሊኖሩ ይገባል፡፡

26. ይሁን እንጂ በናሙና ከተመረጡ በኪራይ ከተያዙ የልማት ድርጅት በኮንትራት ውላቸው ላይ የስጋት መስፈርቶች ተለይተው ባለመቀመጣቸው ችግሮች ተከስተው በውሉ መሠረት ለመፍታት አለመቻሉን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይኸውም በሲሌ እርሻ ልማት የመንግስት ይዞታ ላይ በአካባቢው ነዋሪዎች ህገ ወጥ የመሬት ወረራ፣ የቤት ግንባታ እና የመሬት ሽሚያ ችግር የተፈጠረና የመፍትሄ እርምጃ አለመወሰዱ፤ እንዲሁም በአካባቢው የመስኖ ውሃ ችግር መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ከእርሻ ልማቱ ስራ አስኪያጅ ጋር ከተደረገ ቃለ ምልልስ ለማወቅ ተችሏል፡፡

27. እንደዚሁም የአርባምንጭ እርሻ ልማት መሬት ለትምህርት ቤትና ለሌሎች አገልግሎቶች ተቆራርጦ እየተሰጠ በመሆኑና የከተማ መስተዳደሩ በሚያደርገው የማስፋፊያ ሥራ ምክንያት የእርሻ ልማቱ በሥራ ዕቅዱ መሰረት መሥራት የተቸገረ መሆኑን ከእርሻ ልማቱ ስራ አስኪያጅ እና ከሠራተኛ ማህበር ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ተገልጿል ፡፡

28. ስለሁኔታው የሰሜን ኦሞ እርሻ ልማት የቦርድ አባል ተጠይቀው ችግር መኖሩን ተቀብለዋል፡፡

29. የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በሁለቱም እርሻ ልማቶች ችግሩ በስራ እቅድ አፈጻጸማቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳደረ መሆኑን የሚያመላክት ሪፖርት እንዳልቀረበ እና ኤጀንሲው ለተፈጠሩ ችግሮች በየጊዜው ምላሽ ለመስጠት ጥረት አንዳደረገ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም የኤጀንሲው ሃላፊዎች በመጨረሻ ሪፖርት ላይ በሰጡት አስተያየት ከውሃና መሬት ጋር የተያያዙ ችግሮች ሲያጋጥሙ ኤጀንሲው ችግሮቹን ከክልሉ መስተዳድር አካላት ጋር ሲፈታ መቆየቱንና እንዲያውም ከሊዝ በፊት ከነበረው በጣም የተሻለ ሁኔታ እንዳለ የሚታወቅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

30. በኮንትራት የውል ስምምነት ሰነድ ላይ የስጋት መጠቀሚያ መስፈርቶች አስቀድመው ባለመጠቀሳቸው የሚፈጠሩ ችግሮች ለእርሻ ልማቶቹ የሥራ እንቅስቃሴ ማለትም የሥራ ዕቅድ ተፈፃሚነት እንቅፋት የሚሆኑበት ሁኔታ እና የሥራ ዕቅድ አፈፃፀም መዘግየት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

<u>በጋራ ልማት እና በኪራይ የሚተዳደሩ ድርጅቶችን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እና የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች መስራታቸውን በተመለከተ</u>

31. በጋራ ልማት እና በኪራይ ለተያዙ የልማት ድርጅቶች ባለሃብቱ በሚያቀርበው የሥራ ዕቅድ እና የአፈጻጸም ሪፖርት ላይ የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ እቅድ እንዲኖረውና ተግባራዊ እንዲያደርግ የሚያስገድድ የአሰራር ስርዓት ሊኖር እና ተፈጻሚ ሊሆን እንዲሁም በአከባቢውና በመሬት ላይ የሚያደርሱት አሉታዊ ተጽዕኖ ሊገመገም ይገባል፡፡

32. ይሁን እንጂ በኦዲቱ፣ ባለሃብቱ በሚያቀርበው የሥራ ዕቅድ ላይ የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ እቅድ እንዲኖረው የሚያስገድድ የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋቱ፣

- የአቢጃታ ሀይቅ ቀድሞ ከነበረበት ይዞታ መጠኑ እየቀነሰ መምጣትና የውሃው መጠን መሸሽ እንዲሁም በሀይቁ ውስጥ የነበሩ የዓሣ ዝርያዎች መጥፋት በአክሲዮን ማህበሩ የሥራ እንቅስቃሴ ምክንያት ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ አክሲዮን ማህበሩ እና የዞኑ ግብርና ፅ/ቤት ተጠይቀው በጥናት የተደገፈ ማስረጃ ሊያቀርቡ አልቻሉም፡፡
- እንደዚሁም፣ ለኦዲቱ በተደረገው የመስክ ጉብኝት፣ በሲሌ እርሻ ልማት እና በአርባ ምንጭ እርሻ ልማት የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች እና የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ በስራ እቅዱ ውስጥ ተካተው በተቀናጀ መልኩ አለመሰራታቸውን እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች በሪፖርት ልውውጥ እና ዕቅድ አፈፃፀም ላይ አለመካተታቸውን ከድርጅቶች ስራ አስኪያጆች ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡`
- እንዲሁም የአምቦ ውሃ አክሲዮን ማህበር ድርጅት ፍሳሽ ሰንቀሌ (ደቢስ) ወንዝ ውስጥ የሚገባ ሲሆን ይህም ሊያስከትል የሚችለው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ

አለመደረጉን ከአምቦ ውሃ ከተማ መስተዳድር ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

33. ስለሁኔታው የፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በአቢጃታ ሃይቅ ውስጥ ድርጅቱ ወደ ግል ከመዛወሩም በፊት ዓሣ ያልነበረ መሆኑን፤ የአምቦ ውሃም ፍሳሽ በተፈጥሮው ወደ ወንዙ የሚገባ እንጂ ተረፈ ምርት ሆኖ አካባቢውን የሚበክል እንዳልሆነ ገልፀዋል፡፡
34. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ስለጉዳዩ በመውጫ ስብሰባ ተጠይቀው ለአቢጃታ አክሲዮን ማህበር የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ እንደተካሄደ ገልፀው ነገር ግን የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች በልማት ድርጅቶች የስምምነት ሰነዶች ውስጥ ስላልተቀመጡ በዕቅድና ሪፖርት ልውውጥ ውስጥ እንደማይካተቱና ለወደፊቱ የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች ትኩረት እንዲሰጣቸው እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡
35. በኪራይም ሆነ በጋራ ልማት ለሚያዙ የልማት ድርጅቶች በኤጀንሲው የአካባቢ ጥበቃ እንደ አሰራር ስርዓት ተዘርግቶ አስገዳጅ የአካባቢ ጥበቃ ዕቅድ እንዲኖር አለመደረጉ ድርጅቶች ለአካባቢ ጥበቃ ሥራ ትኩረት እንዳይሰጡ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም በአከባቢና በመሬት ላይ ሊደርስ የሚችል ተጽዕኖ አለመገምገሙ እና የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች በዕቅድ ውስጥ አለመካተታቸው የድርጅቶቹ የሥራ እንቅስቃሴ በአካባቢው እና በማህበረሰቡ ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖ እንዳይታወቅ እንዲሁም የተጠናከረ የአካባቢ ጥበቃ ሥራ እንዳይኖር አድርጓል፡፡

<u>**በጋራ ልማትና በኪራይ የተያዙ ድርጅቶች በስራ እቅዳቸው (Business Plan) መሠረት ለመፈጸማቸው የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ**</u>

36. የልማት ድርጅቶች በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ወደ ግል ከተዛወሩ በኋላ በስራ እቅዱ (Business Plan) መሠረት ባለሀብቶች ሥራዎችን እየሰሩ ስለመሆኑ ወጥ የሆነ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ እንዲሁም የተጠናከረ የመስክ ጉብኝት ሊደረግ ይገባል፡፡
37. ይሁን እንጂ የልማት ድርጅቶች በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ወደ ግል ከተዛወሩ በኋላ ድርጅቶችን የገዙ ባለሀብቶች በገቡት ውል እና በስራ ዕቅዱ መሰረት እየሰሩ ስለመሆኑ ክትትል አለመደረጉና አንዳንድ ባለሀብቶች የውል ግዴታቸውን በወቅቱ አለመወጣታቸውን ከባለድርሻ አካላት ጋር የተካሄዱ ውይይቶች ቃለ ጉባኤ እና ከ2004 በጀት አመት የሥራ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡
38. ኤጀንሲው የአቢጃታ ሶዳ አሽ አክሲዮን ማህበርን ለአጋር ባለሃብቱ በሚያስረክብበት ወቅት የርክክብ ሂደቱ በመዘግየቱ ምክንያት የድርጅቱን ምርት ሥራ እንቅስቃሴ በሥራ ዕቅዱ በተመለከተው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በ2003 ዓ/ም የማስፋፊያና የማሻሻያ ሥራዎች እንዳልተሰሩ ከአቢጃታ ሶዳ አሽ አክሲዮን ማህበር ሥራ አስኪያጅ ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ላይ ለመረዳት ተችሏል፡፡

39. ስለሁኔታው ለፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በተደረገ ቃለ መጠይቅ በተሰጠ መልስ፤ ችግሩ የተከሰተው ለአክስዮን ማህበሩ የስራ እና የንግድ ፈቃድ ለማውጣት በተፈጠረ መዘግየት መሆኑን ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የርክክቡ መዘግየት የተከሰተው የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ረጅም ጊዜ በመፍጀቱና ከጥናቱም መጠናቀቅ በኋላ የማስፋፊያ ስራዎች በተወሰነ መልኩ መዘግየት እንደታየባቸው አስረድተዋል፡፡

40. ይሁን እንጂ ችግሩ የተከሰተው የልማት ድርጅቶችን ከግል ባለሃብቶች ጋር በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ለመስጠት አሸናፊው ድርጅት ታውቆ ኤጀንሲው ውል ከመፈራረሙ በፊት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን አስቀድሞ ካለማጠናቀቅ ነው፡፡ በመሆኑም በአክሲዮን ማህበሩ የምርት ሂደት ላይ በሥራ ዕቅዱ መሠረት እንዳያመርት ተጽዕኖ ሊፈጠር ችሏል፡፡

41. በሌላ በኩል የሲሌ እርሻ ልማት በቢዝነስ ፕላኑ መሠረት የ2002 በጀት አመት ዕቅድ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብና የእርሻ ልማቱ ተከራይ በቢዝነስ ፕላኑ መሰረት ግዴታውን መወጣት ይችል ዘንድ አቅም እንዲፈጥር ቢወሰንም አለመፈፀሙን ከታህሳስ 17 ቀን 2002 ዓ/ም የቦርድ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ቁጥር 191 እና የሲሌ እርሻ ልማት መስከረም 9 ቀን 2002 ቦርድ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ቁጥር 188 ላይ ለመረዳት ተችሏል፡፡

- በተጨማሪም የሲሌ እርሻ ልማት ተከራይ የሆነው ሉሲ እርሻ ልማት ድርጅት ከሀምሌ 1/2003 እስከ ታስሳስ 30/2004 ያለው የሥራ ዕቅድ እና አፈፃፀም ሲታይ ሙዝ 7840 ኩንታል ለማምረት አቅዶ 2378 ኩንታል (30%)፣ ጥጥ 17070 ኩንታል ለማምረት አቅዶ 7167 ኩንታል (42%)፣ በቆሎ 4500 ኩንታል ለማምረት አቅዶ 1060 ኩንታል (24%)፣ የተባዘተ ጥጥ 6315 ኩንታል ለማምረት አቅዶ ምንም (0%) እና የጥጥ ዘር 9730 ኩንታል ለማምረት አቅዶ ምንም (0%) አላመረተም፡፡ እንዲሁም ተከራዩ በ2003 ዓ/ም የምርት ዘመን ብር 633 ሺህ ለማትረፍ አቅዶ የብር 1445 ሺህ ኪሳራ ስላስመዘገበ በ 228% የኪሳራ አፈፃፀም ማሳየቱን በሰኔ 2004ዓ/ም ከተደረገ የቢዝነስ ፕላን አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የሲሌ እርሻ ልማት ድርጅት በሬድ ስፔክል ኢትዮጵያ ትሬዲንግ ተይዞ በነበረበት በታህሳስ ወር 2002 ዓ/ም የተመረተ 954.4 ኩንታል በቆሎ እና 136 ኩንታል ማዳበሪያ በመጋዘን ተከማችቶ የሚገኝ ሲሆን ከአንድ አመት በላይ በመጋዘን በመቆየቱ በሙቀትና ቅዝቃዜ መፈራረቅ፣ በአቧራና በአያያዝ ጉድለት እንዲሁም በነቀዝ ምክንያት የተጠቃ በመሆኑ ለምርጥ ዘር እንደማይሆን፤ በተጨማሪም በመጀመሪያው የውል አመት ማለትም ከ23/2001 እስከ መጋቢት 23/2002 ዓ/ም መከናወን የነበረበት 600 ሄክታር ለጥጥ ማምረቻ የሚሆን መሬት ዝግጅት፣ 110 ሄክታር የፍራፍሬ ማልሚያ መሬት ዝግጅት ሙሉ ለሙሉ እንዳልተከናወነ በሬድ ስፔክልድ

ኢትዮጵያ ትሬዲንግ እና በፐ/መ/ል/ድ/ተ/ኤጀንሲ መካከል የተፈፀመውን የኪራይ ውል አፈፃፀም በተመለከተ የተደረገ ልዩ የኦዲት ምርመራ ላይ ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ከመጋቢት 23/2001 እስከ መጋቢት 23/2002 ዓ/ም 6,000 ኩንታል ቦሎቄ ፣ 30,000 ኩንታል በቆሎ፣ 15,000 ኩንታል ጥጥ፣ 10,000 ኩንታል ሙዝ እንዲመረት ውል ቢገባም ቦሎቄና ጥጥ ምንም ያልተመረተ ሲሆን በቆሎ 4,000 ኩንታል መመረቱ እንዲሁም የሙዝ ምርት መጠንን ማወቅ እንዳልተቻለ ከዚሁ መረጃ ላይ ለማየት ተችሏል፡፡

42. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ የአሁኑ የሲሌ እርሻ ልማት ተከራይ የሆነው ሉሲ እርሻ ልማት በመጀመሪያ የውል ዓመት አፈጻጸሙ የተጠበቀውን ያህል እንዳልነበረና ለዚህም ምክንያቱ አልሚው የእርሻ ጊዜው በተጣበበት ወቅት የሊዝ ውል በመዋዋሉ እንዲሁም የእርሻ መሳሪያዎችን ለማጓጓዝ ጊዜ ስለወሰደበት መሆኑን አስቀምጠዋል፡፡ በተጨማሪም የሲሌ የበፊት ተከራይ ባሳየው ዝቅተኛ አፈጻጸም ውሉ እንዲቋረጥ እንደተደረገና ጉዳዩ በፍርድ ቤት የተያዘና በሂደት ላይ ያለ በመሆኑ የተመረተውን ምርት መሸጥም ሆነ ማስተላለፍ አግባብ ባለመሆኑ ምርቱ ቀድሞ የነበረበት መጋዘን ውስጥ እንዲቀመጥ መደረጉንና የፍርድ ቤት ውሳኔ እንደተላለፈም በውሳኔው መሰረት ተገቢው እንደሚፈጸም ገልፀዋል፡፡

43. በጋራ ልማት በተያዘው ሆራይዘን አዲስ ጎማ አክሲዮን ማህበር እ.ኤ.አ. በ2010 ብር 28,817,063 ትርፍ ያሳየና በቀጣይ አመት በ2011 ደግሞ ብር 2,065,335 ትርፍ እንዳገኘ ኦዲት ከተደረገ በትርፍና ኪሳራ ሂሳብ መግለጫ (Income statemenet) የተመለከተ ሲሆን ከፍተኛ የትርፍ መቀነስ ያሳየ መሆኑን ከሂሳብ መግለጫዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ሆኖም የብር 26,751,728 ትርፍ መቀነስ መታየቱ ኤጀንሲው እንደ ትርፍ ድርሻ ተጋሪነቱ ሊያገኝ ይገባ የነበረውን የትርፍ ድርሻ ቀንሶታል፡፡

44. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ችግሩ የተከሰተው በወቅቱ በነበረው የአስተዳደር ለውጥና የግብዓቶች ዋጋ መጨመር ምክንያት መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በተጨማሪም ድርጅቱ በተጠቀሰው በጀት ዓመት ከማኔጅመንት፣ ከዲቫሎዌሽን፣ ከተፎካካሪ ምርቶች መስፋትና ከማስፋፊያ ስራዎች ጋር የተያያዙ ችግሮች እንደነበሩበትና ችግሮቹን ለመቅረፍ የማኔጅመንት ለውጥን ጨምሮ እርምጃዎች እየተወሰዱ እንደሚገኙና እንደ አጠቃላይም ኤጀንሲው የስራ ዕቅድ አፈፃፀምን በተመለከተ ክትትል እንደሚያደርግና ሊሻሻል እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

45. በዚህም መሰረት ባለሀብቶች በሥራ ዕቅዳቸው መሰረት እየሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ ወጥ የሆነና የማያቋርጥ የአፈፃፀም ክትትል እና የመስክ ጉብኝት አለመደረጉ የተለያዩ በኪራይና በጋራ ልማት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሥራ ዕቅድ በተያዘለት ጊዜ ተፈፃሚ እንዳይሆን እያደረገ ይገኛል፡፡

<u>በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች የቦርድ ጽ/ቤት በየሶስት (3) ወሩ ስለስራ ሂደቱ ለኤጀንሲው ሪፖርት ማቅረቡን በተመለከተ</u>

46.የተከራይ ድርጅት የቦርድ ጽ/ቤት በየሶስት (3) ወሩ ስለስራ ሂደት ለኤጀንሲው ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

47.ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- በሲሌ እርሻ ልማት የውል ሰነዱ በሚያዘውና ስምምነት ላይ በተደረሰው መሰረት ወርሃዊ ሪፖርቶች በወቅቱ ማለትም በየሶስት ወሩ እንዲላኩ ቢወሰንም አለመፈፀሙን ከሰሜን ኦሞ እርሻ ልማት ድርጅት ቦርድ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ቁጥር 213 እና 187 ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የአርባምንጭ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ተከራይ የነበረው ናሪን ኦርሜ ቴክስታይል ግሩፕ በ1998 ዓ/ም (እ.አ.አ ህዳር 2005) ድርጅቱን ተረክቦ ሥራ ከጀመረ ከ3 ወራት በላይ አልፎ የነበረ ቢሆንም ወርሃዊም ሆነ የሩብ አመት ሪፖርቶች ለዳይክተሮች ቦርዱ ማቅረብ እንዳለበት በውል ስምምነት ሰነድ አንቀጽ 6.13 ተጠቅሶ ሳለ ሪፖርቶች ወቅታቸውን ጠብቀው አለመቅረባቸውን ከአርባምንጭ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር የዳይሬክቶሮች ቦርድ መደበኛ ስብሰባ ቁጥር 045 ቃለ ጉባኤ ላይ ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ሬድ ስፔክልድ ኢትዮጵያ ትሬዲንግ የሲሌ እርሻ ልማትን ተከራይቶ ሥራ ከጀመረበት ከመጋቢት 23/2001 ዓ/ም ጀምሮ ውሉ እስከተቋረጠበት ሚያዝያ 1/2002 ዓ/ም ድረስ ወርሀዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት በውሉ መሰረት ለኤጀንሲው ማቅረብ የነበረበት ቢሆንም በ2001 ዓ/ም ሚያዝያ እና ነሀሴ፣ በ2002 ዓ/ም መስከረም፣ ጥቅምትና ጥር ወራት በቀር ተከታታይ ሪፖርት የተላከበት ሁኔታ አለመኖሩን በኤጀንሲው እና በሬድ ስፔክልድ ኢትዮጵያ ትሬዲንግ መካከል የተፈፀመውን የኪራይ ውል አፈፃፀም በተመለከተ ከተደረገ ልዩ ምርመራ ሪፖርት ላይ ለመረዳት ተችሏል፡፡

48. ስለሁኔታው የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የሪፖርት ወጥነት ችግር እንዳለና በቀጣይ ችግሩ እንዳይከሰት ለማድረግ ኤጀንሲው ጥረት እያደረገና ችግሩ እየተፈታ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

49.የልማት ድርጅቶችን የተከራዩ ባለሃብቶች ወጥ የሆነ፤ ውልን እና የሥራ እቅድን መሰረት ያደረገ ሪፖርት ለቦርድ አለማቅረባቸው ቦርዱ ለኤጀንሲው ወጥ ሪፖርት እንዳያቀርብ እና ኤጀንሲውም የልማት ድርጅቶች በሥራ ዕቅዳቸው መሠረት ለመፈጸማቸው እንዳይከታተል ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችን ከግል ባለሃብቶች ጋር ለማልማት ከያዘው ዓላማ አንፃር ተቀባይነት የለውም፡፡

በጋራ ልማት እና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሂሳብ መግለጫዎች (ሪፖርቶች) በወቅቱ መዘጋጀታቸውንና ኦዲት መደረጋቸውን በተመለከተ

50. በጋራ ልማት ኢንቨስትመንትና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሂሳብ ሪፖርቶች የትርፍና ኪሳራ ሪፖርት (Income statemenet) እና የሀብት እና እዳ መግለጫ (Balance sheet) ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ሊቀርብና ፈቃድ ባለው የኦዲት ተቋም ኦዲት ሊደረግ ይገባል፡፡
51. ይሁን እንጂ BM (ቢኤም) ኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት የተያዘው በ2002 ዓ/ም ቢሆንም የሂሳብ መግለጫዎች ለኤጀንሲው አለመላኩን እና በገለልተኛ ኦዲተሮች ኦዲት አለመደረጉን በኦዲቱ ለማየት ተችሏል፡፡
52. ስለሁኔታው ለድህረ ፕራይቬታይዜሽን ቡድን በተደረገ ቃለ መጠይቅ በተሰጠው መልስ ኦዲት የማያስደርግ ድርጅት አለመኖሩንና BM ኢትዮጵያ ከተቋቋመ አጭር ጊዜ በመሆኑና በመቋቋም ሂደት ላይ ስለዘገየ የኦዲት ሪፖርቱ አለመውጣቱንና በሂደት ላይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም የኤጀንሲው ኃላፊዎች በመጨረሻ ሪፖርት ላይ በሰጡት አስተያየት አክሲዮን ማህበሩ ከተቋቋመ በኋላ የሰው ኃይልና የስራ ማስኬጃን ጨምሮ እንጥልጥል ጉዳዮች ስለነበሩበት ችግሮቹ እንደታዩበትና አሁን ግን ጉዳዮቹ የተፈቱ በመሆኑ የድርጅቱ ሂሳብ እንዲዘጋና እንዲመረመር እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡
53. በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት እና በኪራይ የሚያዙ የልማት ድርጅቶች በገለልተኛ ኦዲተሮች ኦዲት አለመደረጋቸውና የፋይናንስ ሪፖርታቸውን መደበኛ በሆነ መልኩ ለኤጀንሲውም ሆነ ለቦርድ አለማቅረባቸው ትክክለኛውን የድርጅቶቹን የትርፍ እና ኪሳራ ሁኔታ ለማወቅ ካለማስቻሉም በላይ የመንግስትን የትርፍ ድርሻ ክፍያን በወቅቱ ገቢ እንዳይደረግ ያደርጋል፡፡

በኪራይ ከተያዙ የልማት ድርጅቶች የሚፈለግ ያልተከፈለ የኪራይ እና ሌሎች የመንግስት እዳዎችን እንዲሁም ውል ቢቋረጥ አፈጻጸሙ በስምምነት ሰነዱ መሰረት መሆኑን በተመለከተ

54. ኤጀንሲው በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ከግል ባለሀብቱ ጋር በሚያስተዳድራቸው ድርጅቶች ስር ያለው የኃላፊነትና የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሁም ውል ቢቋረጥ አፈጻጸሙ በስምምነት ሰነዱ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡
55. ይሁን እንጂ አርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበርን ቀደም ብሎ በ1992 ዓ/ም (እ.አ.አ ጥቅምት 2000) ተከራይቶ የነበረው አቲላ ይልድሪም የተባለው ግለሰብ የተለያዩ የመንግስት ዕዳዎች ማለትም የአላቂ እቃዎች ክምችት ዋጋ፣ የኪራይ ክፍያ፣ የኦቨር ድራፍት ክፍያ፣ የሰራተኞች ኢንሹራንስ፣ የስልክና የውሃ ክፍያ እንዲሁም የወለድ ክፍያን ጨምሮ በባለሀብቱ ብር 25,579,395.55 ያልተከፈለ መሆኑን መስከረም 1998 ዓ/ም ቁጥር ዲ.ቦ /111/98 በአርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር የቀረበ የሊዝ ሰነድ ላይ ከቀረበ ፅሁፍ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ ገንዘብ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ታህሳስ ወር 2005 ዓ/ም ድረስ አልተሰበሰበም፡፡

- ከዚሁ ጋር በተያያዘ የአክሲዮን ማህበሩን በ1998 ዓ/ም ተከራይቶ የነበረው ናሪን ኦርሚ ቴክስታይል ግሩፕ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ለሥራ ማስኬጃ ብድር ብር 8 ሚሊዮን በየካቲት 30/1998 ዓ.ም የተሰጠው ሲሆን ከ1/07/99 ዓ/ም ጀምሮ በየሶስት ወሩ ብር 1 ሚሊዮን የመክፈል ግዴታ ቢኖርበትም እስከ ህዳር 2005 ዓ/ም ክፍያ ያልጀመረ መሆኑን ለአክሲዮን ማህበሩ ከተፃፈ ደብዳቤ ቁጥር 100/154/7/119/99 ለማወቅ ተችሏል፡፡
- እንዲሁም ይኸው ተከራይ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ለመለዋወጫ መግዣ እና የቆሙ መሳሪያዎች ተጠግነው ማምረት እንዲጀምሩ የተሰጠውን ብር 8 ሚሊዮን ለተባለው ሥራ ስለ መዋሉ እና ስላስገኘው ውጤት ሪፖርት ያላቀረበ መሆኑን ለአክሲዮን ማህበሩ ከተፃፉ ደብዳቤዎች ቁጥር 100/154/7/119/99 እና 100/154/8/127/2000 ላይ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በተጨማሪም ይህ ተከራይ በገባው የውል ግዴታ መሰረት ኃላፊነቱን መወጣት ባለመቻሉ መክፈል የነበረበትን የኪራይ ክፍያ 760 ሺህ የአሜሪካን ዶላር ባለመክፈሉ በየካቲት 2001 ዓ.ም የኪራይ ውሉ እንዲቋረጥ መደረጉን ለአክሲዮን ማህበሩ ከተፃፉ ደብዳቤዎች ቁጥር 100/154/10/180/2001 እና 100/154/10/181/2001 ለማየት ተችሏል፡፡

56.አርባምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ሁለት ጊዜ ለተለያዩ ባለሃብቶች በኪራይ ተሰጥቶ ውጤታማ ሊሆን አልቻለም፡፡

57.የአዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካን በ1998 ዓ.ም ተከራይቶ የነበረው ናሪን ኦርሚ የኪራዩን ገንዘብ በውሉ መሰረት በወቅቱ አለመመለስ፣ በውሉ መሰረት የመሳሪያዎች ዕድሳት አለመከናወን፣ የተለያዩ ዕዳዎች ማለትም፤የኤክሳይዝ ታክስ (ብር 23.5 ሚሊዮን)፣ የኤሌክትሪክ ክፍያ (ብር 4.1 ሚሊዮን)፣ የቫት ክፍያ (ብር 5.6 ሚሊዮን)፣ የሀገር ውስጥ ገቢ (ብር 3.2 ሚሊዮን) እና የጡረታ ገንዘብ (ብር 474 ሺህ) ያልተከፈሉ መሆኑ ከአዋሳ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ዳሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ቃለ ጉባዔ ቀን 18/09/2000 ላይ ለመረዳት ተችሏል፡፡

- ከዚሁ ጋር በተያያዘ ባለሀብቱ በገቡት ውል መሰረት አክሲዮን ማህበሩን ለማልማት ባለመቻላቸውና ሃላፊነታቸውን በአግባቡ ሊወጡ ባለመቻላቸው የሊዝ ውሉ እንዲቋረጥ በማድረግ አክሲዮን ማህበሩ መንግስት እንዲረከበውና ባለሃብቱ ለተጠቀሙበት የመንግስት ሀብት ዋጋ (በንብረት ርክክብ ወቅት የታየ ጉድለት) ብር 37, 870,833 እና በወቅቱ ያልተከፈለ የሊዝ ክፍያ የአሜሪካ ዶላር $1,978,461.66 በድምሩ ብር 72 ሚሊዮን ያልተከፈለ እዳ መኖሩን ለገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከተፃፈ ደብዳቤ ቁጥር 300-220/356/10 እና የኤጀንሲው ጠበቃ ለግልግል ዳኝነት ጉባዔ ካቀረበው የክስ መረጃ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

58.ሬድ ስፔክልድ የተባለው የሲሌ እርሻ ልማት ድርጅት ተከራይ በገባው የውል ስምምነትና የሥራ ዕቅድ መሰረት ሥራውን እያከናወነና ግዴታዎቹንም እየተወጣ ያልነበረ መሆኑን በኦዲት ዳይሬክቶሬት የውስጥ ማስታወሻ በቀን 1/2003 በቁጥር ኦዳ 0161/2003 ከተጻፈ

ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ተከራይ ግዴታዎቹን ባለመወጣቱ ምክንያት ለወደፊቱ ሊጣል የሚችለውን ቅጣት የመሸፈን ሃላፊነት ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከተረከበው ንብረት ውስጥ የተጠቀመውና በውሉ መሰረት መክፈል ሲገባው ያልከፈላቸው ግዴታዎች ማለትም የሰራተኛ ደሞዝ፣ የሥራ ግብር፣ የጡረታ ክፍያ፣ የቤተሰብ ህክምና መዋጮ፣ የሰራተኛ ማህበር መዋጮ፣ የመድን ዋስትና መዋጮ፣ የአላቂ እቃዎች ዋጋ እና የኪራይ ክፍያ በድምሩ ብር 1,685,090.22 ያልተከፈለ ዕዳ ያለበት መሆኑን በኤጀንሲው እና በሬድ ስፔክልድ ኢትዮጵያ ትሬዲንግ መካከል የተፈፀመውን የኪራይ ውል አፈፃፀም በተመለከተ በታህሳስ 2003 ዓ/ም ከተደረገ ልዩ ምርመራ ሪፖርት ላይ ለመረዳት ተችሏል፡፡

- በተጨማሪም ይህ ድርጅት የሰሌዳ ቁጥር 3-ኢት04858 እና የሞባይል መስመር 0911388915 ከኖኪያ ቀፎ ጋር ተረክቦ ያልመለሰ መሆኑን ከደብዳቤ ቁጥር 60/283/4/57/2004 ለመረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም በሥራ ዕቅዱ መሰረት ያስቆፈራቸው አራት ጥልቅ ጉድጓዶች በባለቤትነት ጥያቄ ምክንያት ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ታሽገው በመቀመጥ ጥቅም ላይ ሊውሉ አለመቻላቸውን ከፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች እና ከሲሌ እርሻ ልማት ስራ አስኪያጅ ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

59. ስለሁኔታው የፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ መኪናው እንዲመለስ ክስ ተመስርቶና ክትትል ሲደረግ ቆይቶ መኪናውን ማስመለስ የተቻለ ሲሆን ያለበትን ሌሎች እዳዎች ለማስመለስ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ተይዞ ክትትል እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡
60. ለኦዲት ሪፖርቱ በኤጀንሲው ኃላፊዎች በተሰጠው ምላሽ ከኦዲተሮች ጋር የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ ሞባይሉ እንደተመለሰ ገልፀዋል፡፡
61. ስለ ጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ባስቀመጡት ሃሳብ ባለሃብቶቹ እዳቸውን እንዲከፍሉ ተደጋጋሚ ጥያቄ በማቅረብና በመወያየት እልባት ለመስጠት ጥረት ቢደረግም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በውሉ መሰረት ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት ጉባኤ እንዲታይ ዳኞች መሰየማቸውን እንዲሁም ከላይ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠንም በፍርድ ቤት የተወሰነ እንዳልሆነና ፍርድ ቤቱ የሚወስነውን የገንዘብ መጠን ይዘው ወደ አፈጻጸም እንደሚሄዱ አስረድተዋል፡፡
62. ድርጅቶቹ የኪራይ ክፍያንና ሌሎች የመንግስት ዕዳዎችን በውሉ መሰረት በወቅቱ አለመክፈላቸው መንግስት በወቅቱ ገቢ እንዳያገኝ ያደርጋል፡፡ ድርጅቶቹ በገቡት ውልና የስራ ዕቅድ መሰረት ስራቸውን አለማከናወናቸው እና የውል መቋረጥ ሲከሰት በተገባው ውለታ መሰረት ተፈጻሚ አለመሆኑ ባለሃብቶች መክፍል የሚገባቸውን ክፍያ ሳያጠናቅቁ እንዲወጡና የመንግስት ሃብት ብክነትና መጥፋት እንዲኖር አድርጓል፡፡

በጋራ ልማት እና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች የትርፍ ድርሻ (dividend) እና የኪራይ ክፍያን በተመለከተ

63.የልማት ድርጅቱ በገባው ውለታ መሰረት በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ለተያዙ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የኪራይ ክፍያና የመንግስትን የትርፍ መዋጮ በወቅቱ ሊከፍል ይገባል፡፡

64.የአምቦ ውሃ አክሲዮን ማህበር አጋር የሆነው ድርጅት ሳብ ሚለር ኃ/የተ/የግ/ማህበር እስከ እ.ኤ.አ ህዳር 2010 መክፈል የነበረበትን የድርጅቱን እዳ ብር 4,499,309 እስከ ታህሳስ 2005 ዓ/ም ድረስ አለመክፈሉን ከኮርፖሬት ፋይናንስና ፈንድ አስተዳደር ከተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

65.ስለሁኔታው የድህረ ፕራይቬታይዜሽን ቡድን ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የመንግስት ትርፍ ድርሻ መዋጮ በምንም ዓይነት ሳይከፈል ሊቀር እንደማይችልና ድርጅቱ ዕዳውን በመክፈል ላይ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

66.የሲሌ እርሻ ልማት ድርጅት ተከራይ ሉሲ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የኪራይ ክፍያ እና ወለድ ብር 1.711 ሚሊዮን እስከ ታህሳስ 2005 አለመክፈሉን ከፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ከቀረበ መረጃ ለማየት ተችሏል፡፡ በዚሁ ድርጅት የኪራይ ክፍያ መጓተት ከመኖሩም በላይ ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ክፍያ፣ የሊዝ ኪራይ ክፍያ እና ሌሎችም የመንግስት ግዴታዎች በወቅቱ ተፈጽሞ ወጤቱ እንዲገለጽለት ቦርዱ ቢወስንም አለመፈፀሙን ከሰሜን ኦሞ እርሻ ልማት ድርጅት ቦርድ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ቁጥር 207 እና 193 ለመረዳት ተችሏል፡፡

67.የአደሌ እርሻ ልማት ድርጅት ተከራይ የሆነው አፊያ የምግብ ኮምፕሌክስ የሶስት ሩብ አመት የኪራይ ክፍያ ብር 1,006,416.8 እስከ ታህሳስ 2005 ዓ/ም ያልከፈለ መሆኑ ከፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ከተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

68.ስለሁኔታው የፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ የሲሌ እርሻ ልማት ተከራይ ባለሃብት ሉሲ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ክፍያውን እንዲፈፅም በአካል ጭምር ተጠርቶ የተነገረው ሲሆን የክፍያው መዘግየት የተፈጠረው በአገር አቀፍ ደረጃ በጥጥ ምርት ዋጋ ችግር ምክንያት መሆኑንና፤ ላለመክፈሉ በቂ ምክንያት ያለው ከመሆኑም በላይ ጊዜው አጭር በመሆኑ ችግሩ ትልቅ የሚባል እንዳልሆነና በቅርቡ እንደሚከፍል እንጠብቃለን ብለዋል፡፡ በተጨማሪም ከነበረበት የ3 ጊዜ ክፍያ አንዱን ብቻ እንደከፈለና ቀሪውን በጥር ወር እንዲከፍል እንደሚደረግ አስረድተዋል፡፡ የአደሌ እርሻ ልማትን በተመለከተ የውል ጊዜው በመጠናቀቁ ተከራዩ ያለበትን ዕዳዎች ሳይከፍል ያመረተውን 12000 ኩንታል ምርት እንዳይተላለፍ መደረጉን የኤጀንሲው ኃላፊዎች በመጨረሻ ሪፖርት ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

69.ባለሃብቶች የኪራይ እና የመንግስት የትርፍ ድርሻ ክፍያን በውሉ መሰረት በወቅቱ አለመክፈላቸው መንግስት ማግኘት የሚገባውን ገቢ በወቅቱ እንዳያገኝና የውል መቋረጥ በሚከሰትበት ጊዜ ባለሃብቶች እዳቸውን ሳይከፍሉ ጉዳዩ ወደ ክስ እንዲያመራ ያደርጋል፡፡

<u>**ሰንጠረዥ 1፡- በተከራይ እና በአጋር ባለሃብቶች ያልተከፈሉ የመንግስት ዕዳዎች ዝርዝር**</u>

ተራ ቁጥር	የልማት ድርጅቱ ሥም	ተከራይ (አጋር) ባለሃብት	ያልከፈለው የዕዳ መጠን	የዕዳው ዓይነት
1.	አርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ	አቲላ ይልድሪም	ብር 25,579,395.55	የኪራይ ክፍያ እና ሌሎች እዳዎች
2.	አርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ	ናሪን ኦርሚ ቴክስታይል	760 ሺህ የአሜሪካን ዶላር	የኪራይ ክፍያ
3.	አዋሳ ጨርቃ ጨርቅ	ናሪን ኦርሚ ቴክስታይል	ብር 72 ሚሊዮን	የኪራይ ክፍያ እና ሌሎች እዳዎች
4.	ሲሌ እርሻ ልማት	ሬድ ስፔክልድ ኢትዮጵያ	ብር 1,685,090.22	የኪራይ ክፍያ እና ሌሎች እዳዎች
5.	ሲሌ እርሻ ልማት	ሉሲ እርሻ ልማት	ብር 1.711 ሚሊዮን	የኪራይ ክፍያ
6.	አምቦ ውሃ አክሲዮን ማህበር	ሳብ ሚለር	ብር 4,499,309	የድርጅቱ እዳ
7.	አደሌ እርሻ ልማት	አፊያ የምግብ ኮምፕሌክስ	ብር 1,006,416.8	የኪራይ ክፍያ

የልማት ድርጅቶች በኪራይና በጋራ ልማት ከተያዙ በኋላ ያስከተሉት አጠቃላይ ውጤት ኤጀንሲው በተወሰነ የጊዜ ገደብ መገምገሙን በተመለከተ

70. የልማት ድርጅቶች በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ለግል ባለሀብቶች ከተሰጡ በኋላ ፕራይቬታይዜሽኑ ያስከተለውን አጠቃላይ ውጤት ኤጀንሲው በተወሰነ የጊዜ ገደብ መገምገም አለበት፡፡

71. የልማት ድርጅቶች በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ለግል ባለሀብቶች ከተሰጡ በኋላ ፕራይቬታይዜሽኑ ያስከተለውን አጠቃላይ ውጤት ኤጀንሲው ወጥነት ባለው ሁኔታ በተወሰነ የጊዜ ገደብ እንዲገመገም አላደረገም፡፡

72. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በሰጡት መልስ ግምገማው አንድ ጊዜ በ2001 ዓ/ም በውጭ አማካሪ እንዲሁም አንድ ጊዜ በውስጥ ባለሙያዎች የተሰራ መሆኑን እንደ ጥንካሬ እንዲሁም ግምገማው መደበኛ በሆነ የጊዜ ገደብ አለመሰራቱን እንደ ድክመት እንደሚመለከቱት አስረድተዋል፡፡ አሁንም ወደግል በተዛወሩ ድርጅቶች የመጣውን ለውጥ የሚያሳይ ሁለንተናዊ ጥናት ከ UNDP በሚገኝ ድጋፍ ለማካሄድ ጥያቄ ለ UNDP ቀርቦ ተቀባይነትን ማግኘቱንና በቀጣይ ዝርዝር የጥናት ስራ ለመጀመር እንደሚጠበቅ ገልጸዋል፡፡

73. የልማት ድርጅቶች በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ለግል ባለሀብቶች ከተሰጡ በኋላ ፕራይቬታይዜሽኑ ያስከተለውን አጠቃላይ ውጤት ኤጀንሲው መደበኛ በሆነ የጊዜ ገደብ አለመገምገሙ ለቀጣይ አፈፃፀም እርምት ሊወሰድባቸው የሚገቡ ጉዳዮች እንዳይለዩና አጠቃላይ የፕራይቬታይዜሽን ውጤት በጠራ መልኩ እንዳይታወቅ አድርጓል፡፡

በጋራ ልማትና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች ስር ያሉ የኤጀንሲው ንብረቶች አያያዝን በተመለከተ

74. የልማት ድርጅት ወደ ግል ባለሀብት ሲዘዋወር በድርጅቱ ውስጥ ያለ ንብረት ለተከራይ ባለሀብት ተቆጥሮና ተመዝግቦ ሊተላለፍ ይገባል፡፡

75. በአርባ ምንጭ እርሻ ልማት ድርጅት ግቢ ውስጥ አሚባራ እርሻ ልማት የተረከባቸው የተለያዩ ያረጁ ማሽኖች (ዶዘር፣ የበቆሎ መፈልፈያ የመሳሰሉት) ተቀምጠውና ሳር በቅሎባቸው፣ ዝናብና ፀሃይ እየተፈራረቀባቸው መገኘታቸውን እንዲሁም በእርሻ ልማቱ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ አብዛኛዎች መለዋወጫዎች ጊዜ ያለፈባቸው ከመሆናቸው በላይ እናት ማሽኖቻቸው ከጥቅም ውጭ ሆነው የሚገኙ መሆናቸውን በአካል በመገኘት እና በማየት ለመረዳት ተችሏል፡፡

ምስል 1፡- በአርባምንጭ እርሻ ልማት ግቢ ውስጥ ተበላሽተው ቆመው ከሚገኙ ማሽኖች በከፊል

76. ስለሁኔታው ከፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ንብረቶቹ የወዳደቁ እና የተበላሹ ብረታ ብረቶች በመሆናቸው የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን የሚፈልጋቸውና ኮርፖሬሽኑ እንደሚያነሳቸው ያላቸውን እምነት አስቀምጠዋል፡፡
77. በተጨማሪም አሚባራ ሀ/የተ/የግ/ኩባንያ ከመንግስት የተከራየውን ሎደር እንዲሁም ሌሎች ማሽኖች ለ3ኛ ወገን በማከራየት በ2003/2004 ዓ.ም ብር 2,095,581.27 ገቢ ሰብስቦ የተገኘ መሆኑ ከትርፍ እና ኪሳራ የሂሳብ ሪፖርት እና በ14/11/2004 ከተፃፈ የመሳሪያ የኪራይ ውል እና ከእርሻ ልማቱ ስራ አስኪያጅ በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡
78. ስለሁኔታው የኤጀንሲው ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ መረጃውን እንደማያውቁትና ተከራይ የተከራየውን ንብረት ለኤጀንሲው ሳያሳውቅ ለሶስተኛ ወገን ማከራየት እንደማይችል ነገር ግን መንግስት ያከራየውን ንብረት የኪራይ ጊዜ ሲጠናቀቅ ንብረቶቹን ባስረከበበት ሁኔታ እንደሚረከብ ጠቅሰዋል፡፡ እንዲሁም ከሰሜን ኦሞ እርሻ ልማት ሥራ አመራር ቦርድ ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ የልማት ድርጅቶችን የያዙ ባለሃብቶች ማሽኖችን ወይም ንብረቶችን ለሶስተኛ ወገን ሲያስተላልፉ ለቦርዱ የሚያሳውቁበት መንገድ የሌለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

79. የኤጀንሲው ኃላፊዎች በኦዲቱ ሪፖርት ላይ በሰጡት ምላሽ የመንግስት ንብረቶችን ለሶስተኛ ወገን ሲያከራይ የነበረው ተከራይ ጉዳዩን ስለመፈጸሙ ተጣርቶ ማስተካከያ እንደሚወሰድ ገልፀዋል፡፡

80. የአደሌ እርሻ ልማት ተከራይ ባለሃብት የሆነው አፊያ የምግብ ኮምፕሌክስ ከመንግስት በኪራይ የተረከባቸውን የእርሻ መሳሪያዎች እና ማሽኖች ወቅቱን የጠበቀ ተገቢ ጥገና ስላልተደረገላቸው ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

81. ንብረቶች ለተከራየው ድርጅት ሲተላለፉ ተቆጥረው እና ተመዝግበው እንደመሆኑ መጠን በአግባቡ ካልተያዙና ለሦስተኛ ወገን የሚከራዩበት ሁኔታ ካለ የመንግስት ንብረት አለአግባብ ጥቅም ላይ እንዲውል እና እንዲበላሽ ስለሚያደርግ አሰራሩ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

82. እንዲሁም የአርባምንጭ እርሻ ልማት ድርጅት ዓመታዊ የኪራይ ክፍያ ብር 1.3 ሚሊዮን ሲሆን ይህም ማሽኖችን በማከራየት በዓመት ካገኘው ገቢ ብር 2,095,581.27 ያነሰ በመሆኑ የኪራይ ክፍያው መንግስት ማግኘት የሚገባውን ጥቅም እንዳያገኝ ያደረገና ለባለሃብቱ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም እንዲያገኝ ያደረገ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ በመሆኑ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>**በኪራይና በጋራ ልማት እየለሙ የሚገኙ ድርጅቶች ውስጥ ያለ የባለሃብት እና ሰራተኛን ግንኙነት በተመለከተ**</u>

83. በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ መሰረት በድርጅቱ የሥራ ቦታ የደህንነት እና የጥንቃቄ መሳሪያዎች ሊሟሉና በሰራተኛው ጤናና ህይወት ላይ ያሉ አሉታዊ ሁኔታዎች ሊወገዱ ይገባል፡፡

84. ይሁን እንጂ፣

- በአቢጃታ ሶዳ አሽ አክሲዮን ማህበር ለእያንዳንዱ ሠራተኛ የመከላከያ መሳሪያ አለመኖር ለመጥቀስ ያህል የቆዳ እና የትንፋሽ መከላከያ በበቂ ሁኔታ አለመገኘት እንዲሁም Ear plugs ለሠራተኞች አለመስጠት ዋናው ችግር ሲሆን፣ ያሉትን የጥንቃቄ መሳሪያዎች ለመጠቀም የሚያስችል ስልጠና ለሠራተኞች ያለመስጠቱ ሌላው ችግር መሆኑን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ክሊነር ፕሮዳክሽን ማእከል በከለሰው የአካባቢ ኦዲት ርፖርት (Revised Environmental Audit Report) ላይ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በአክሲዮን ማህበሩ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ በበቂ ሁኔታ እንደሌለና ያለውም ከጊዜው ጋር ያልተጣጣመ መሆኑን እንዲሁም አስቸኳይ ጉዳዮችን ማለትም የእሳትና ሌሎች አደጋዎችን ለማጥፋት እንዲቻል የተፃፈ መመሪያ እንደሌለ በዚሁ ሪፖርት ተገልጿል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በፋብሪካው ለሚሰሩ ሠራተኞች የሚሰጠው ጫማና መሸከሚያ አመቺ ባለመሆኑ ሠራተኛው የማይጠቀምበት ሁኔታ መኖሩን በአክሲዮን ማህበሩ ለሚገኝ ሰራተኛ ማህበር ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

- አርባ ምንጭ እርሻ ልማት ድርጅት ስር ባለው ጥጥ መዳመጫ ፋብሪካው ውስጥ ወደ ከፍታ የፋብሪካው ማሽን ላይ ለሚወጡ ሰራተኞች የደህንነት ቀበቶ እና የደህንነት መሳሪያ እንደሌለ እንዲሁም የእሳት ማጥፊያ መሣሪያም ሆነ እሳትን የሚያጠፉ ባለሙያ አለመኖሩን የአርባ ምንጭ እርሻ ልማት ድርጅት የሰራተኛ ማህበር አስረድተዋል፡፡
- በቢኤም ኢትዮጵያ የሠራተኛ የደህንነትና ጥቅማ ጥቅሞች አለመሟላት ምክንያት ሠራተኞች ጉዳዩን ፍርድ ቤት ያደረሱበት ሁኔታ መኖሩን ለቢኤም ኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ሰራተኛ ማህበር ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

85. በጡረታ ወይም በግል ምክንያት ሥራቸውን መልቀቅ ለሚፈልጉ ሰራተኞች የሥራ ዕቅዱንና ውሉን መሰረት ባደረገ መልኩ ጥቅማ ጥቅማቸውን በአግባቡ ማግኘት አለባቸው፡፡ እንዲሁም አንድ የመንግስት የልማት ድርጅት ወደ ግል ባለሀብት ከተዛወረ በኋላ ነባር ሰራተኞች የጡረታና ሌሎች ጥቅማ ጥቅማቸው ሳይነካ በስራው እንዲቀጥሉ ማደረግና ባለሀብቱ ከሰራተኛ ማህበራት ጋር የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ በሚያዘው መሰረት የስራ ግንኙነት እንዲኖረው መመቻቸት ይኖርበታል፡፡

86. ይሁን እንጂ

- የሲሌ እርሻ ልማት የ3 ወራት የሰራተኞች የጡረታ መዋጮ አለመክፈሉን ከሲሌ እርሻ ልማት ስራ አስኪያጅ ጋር ከተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- አርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮንን ተከራይቶ ከነበረው ከሚ/ር አቲላ ይልድሪም ጋር የነበርውን ክርክር በተመለከተ የተሰጠው የፍርድ ቤት ውሳኔና ትዕዛዝ ላይ ለማየት እንደተቻለው በከሳሽና ተከሳሽ መካከል የነበረው የሊዝ ውል ግንቦት 27 ቀን 1993 ዓ/ም የተቋረጠ ስለሆነ ከህዳር 22 ቀን 1994 ዓ/ም ለሠራተኛው ተከፍሏል የተባለው ደመወዝ ብር 274,414.67 ተከሳሽ ለመክፈሉም የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡
- የቢኤም ኢትዮጵያ ድርጅቱ ወደ ግል ባለሀብት በሚዞርበት ወቅት ሠራተኛው እንዲያውቅ የተደረገበት አካሄድ አለመኖሩን ከቢኤም ኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ጋር ካደረግነው ቃለ መጠይቅ የገለጹ ሲሆን፣ ስለጉዳዩ የፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ድርጅቶች ወደ ግል ባለሀብት በሚዞሩበት ወቅት ሠራተኛው እንዲያውቅ የሚደረገበት አካሄድ እንዳለ ገልፀዋል፡፡

87. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ እና በህብረት ስምምነት ሰነዱ ላይ የተቀመጡ ሰራተኛ የደህንነትና የጥንቃቄ መሳሪያዎች መሟላት አለመሟላታቸውን ወጥ በሆነ ክትትል አለመታየቱን እንደ ድክመት እንደሚቀበሉት ነገር ግን በጊዜ ሂደት የተፈጠሩ የአሰሪና ሰራተኛ ችግሮችን ኤጀንሲው ሁለቱን ወገኖች በማገናኘት ለመፍታት ጥረት አድርጎ በብዙዎቹ የተሳካ ውጤት ማግኘቱን አስረድተዋል፡፡ የሰራተኛ ጥቅማ ጥቅም ጉዳይ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በሚኖር ስምምነት የሚወሰን

እንጂ ኤጀንሲው በየጊዜው ጣልቃ እየገባ በባለሃብቶች ላይ ጫና የሚያሳርፍበት አሰራር እንደሌለ በተጨማሪ አስታውቀዋል፡፡

88. በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ መሰረት በድርጅቱ የሥራ ቦታ የደህንነት እና የጥንቃቄ መሳሪያዎች አለመሟላታቸው በድርጅቶቹ ውስጥ የኢንዱስትሪ ሰላም እንዳይሰፍን እና ሰራተኛው ለሥራው ተነሳሽ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም በጡረታ ወይም በግል ሥራቸውን ለሚለቁ ሰራተኞች የሥራ ዕቅዱንና ውሉን መሰረት ባደረገ መልኩ ጥቅማቸው አለመከበሩ እና ተከራዮች የሰራተኛ ደሞዝ ሳይከፍሉ ውል አቋርጠው መጥፋታቸው ሰራተኛው አለአግባብ ለሆነ መንገላታትና ለስራ ተነሳሽነት ማነስ እንደ ምክንያት ሆኗል፡፡ እንዲሁም ኤጀንሲው በልማት ድርጅቶች ዙሪያ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ግልፅ በሆነ መልኩ አለማሳወቁ በሰራተኛው ላይ የስነ ልቦና ዝግጅት እንዳይኖርና ሥራው በፍራቻ በተገቢው መልኩ እንዳይከናወን ያደርጋል፡፡

<u>በጋራ ልማት እና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች ዙሪያ በኤጀንሲው ያለውን የመረጃ ሥርዓት በተመለከተ</u>

89. ኤጀንሲው ከግል ባለሀብቱ ጋር በጋራ ልማት ኢንቨስትመንትና በኪራይ ሊያለማ ያሰባቸውን የልማት ድርጅቶች ሊለይና ሙሉ መረጃን በሚሰጡ መልኩ ማዕከላዊ በሆነ የኤጀንሲው የመረጃ መረብ ላይ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡ እንዲሁም ኤጀንሲው የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና ህብረተሰቡ ወቅታዊ መረጃዎችን እንዲያገኙ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
90. ኤጀንሲው መረጃዎችን የሚያስቀምጥበት የመረጃ መረብ ቢኖረውም እ.ኤ.አ ከ2007 አንስቶ ከግል ባለሃብቱ ጋር በኪራይና በጋራ ልማት የሚያዙ እና ሊያዙ የታቀዱ ድርጅቶችን ዝርዝር፣ እስከ መቼ በግል ባለሃብቱ መያዝ እንደሚችሉ እና በምን ያህል የኪራይ ዋጋ እና የድርሻ መዋጮ የሚሉትን መረጃዎች በግልፅ አለማስቀመጡንና በየጊዜው ወቅታዊ የሚደረግበት ሁኔታ አጥጋቢ ሆኖ አለመገኘቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡
91. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ኤጀንሲው ስለ አሰራሩ ለባለድርሻ አካላት ለማሳወቅ በየጊዜው የሚታተሙ መፅሄቶችንና ብሮሽሮች እንደሚጠቀም ነገር ግን የመረጃ መረቡ ወቅታዊ አለመደረጉ እንደ ችግር ታይቶ እንዲስተካከል እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡
92. ኤጀንሲው መረጃዎችን የሚያስቀምጥበት የመረጃ መረብ ሙሉ መልዕክትን ሊሰጥ በሚችል መልኩ አለመቀመጡንና በየጊዜው ወቅታዊ የሚደረግበት ሁኔታ አለመኖሩ ኤጀንሲው እየተገበረ የሚገኘውን አሰራር እና ሊያለማ ያሰባቸውን ድርጅቶች ባለሃብቱ በቀላሉ እንዳያውቅና የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራምና አፈፃፀሙ በህዝቡ እንዳይታወቅ ያደርጋል፡፡

ክፍል ሦስት
መደምደሚያዎች

ከላይ በኦዲት ግኝቶች ላይ እንደተመለከተው በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ከግል ባለሃብቶች ጋር በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት እያለማ ከሚገኛቸው ድርጅቶች ውስጥ በናሙና ተመርጠው የታዩትን ድርጅቶች በተመለከተ የሚከተሉት መደምደሚያዎች ተሰጥተዋል፡-

93. ለልማት ድርጅቶቹ አጋር ወይም ተከራይ በሚመረጥበት ሂደት ላይ የሥራ ዕቅድ ተፈፃሚነት በተጨባጭ ሳይገመገም በአንፃራዊነት ከሌላው የተሻለ የሥራ እቅድ ያቀረበውን ብቻ ማለትም በኢንቨስትመንት፣ በኤክስፖርት፣ በአቅም አጠቃቀም፣ በቴክኖሎጂና በአሰራር ስርዓት የሚመረጠው የልማት ድርጅት አጋር ወይም ተከራይ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለማስገባት የማይችል፣ የሀገር ውስጥ የኢንደስትሪ ፍላጎትን ከማርካት አልፎ የውጭ ምንዛሪ እንዲድን የማያደርግ ከሆነ በእነዚሁ ነጥቦች መሠረት ተፈጻሚነቱ በተጨባጭ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ወይም የማይችል መሆኑን ለማረጋገጥ የሚጠቀምበት መንገድ በጠንካራና ወቅታዊ ክትትል ካልተደገፈ በቂ ባለመሆኑ ተፈፃሚ የማይሆኑ ዕቅዶች በባለሀብቶች ቀርበው ሊመረጡ ችለዋል፡፡
94. በኪራይ ለሚያዙ ድርጅቶች የእፎይታ ጊዜ ኪራይ ክፍያ መቼ እንደሚከፈል በግልፅ አለመቀመጡ ክፍያው ሳይከፈል የሚቀርበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡
95. የኪራይ መመሪያው በሚያዘው መሰረት ኤጀንሲው እና ተከራይ ድርጅቶች የስጋት መጠቆሚያ መስፈርት በውል ውስጥ ማካተት ካልተቻለ በሥራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮች በውሉ መሠረት ለመፍታት ችግር የሚፈጥር መሆኑ ይህም ለሥራ እንቅስቃሴ እንቅፋት በመሆን የሥራ እቅዱ በተያዘለት ጊዜ እንዳይጠናቀቅ ያደርጋል፡፡
96. ኤጀንሲው ድርጅቶችን በጋራ ልማትና በኪራይ ሲሰጥ በአካባቢ ጥበቃ ላይ የዘረጋውን የአሰራር ስርዓት ድርጅቶቹ በዕቅዳቸው ውስጥ አስገብተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ባለማስገደዱ እና ድርጅቶቹም ወጥ በሆነ መልኩ ከሥራቸው ጋር ጎን ለጎን የአካባቢ ጥበቃ ሥራንና የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ተግባራዊ ማድረግ ባለመቻላቸውና የተለያዩ የአካባቢ ችግሮች እየደረሱ እንደሆነ የሚጠቁሙ ነገሮች ታይተዋል፡፡
97. ኤጀንሲው በጋራ ልማትና በኪራይ ለተያዙ ድርጅቶች ክትትልና የመስክ ጉብኝትን በተመለከተ የአሰራር ስርዓት የዘረጋ ቢሆንም ወጥ በሆነ፣ በውሉ እና በሥራ ዕቅዱ መሰረት ከተከራይ ቦርድ ጽ/ቤትና ከአጋር ድርጅቶች የአፈጻጸም ሪፖርት ወቅቱን ጠብቆ የማይቀርብለት መሆኑ ኤጀንሲው የድርጅቶችን ሁኔታ በሥራ ዕቅዳቸው መሰረት እየፈጸሙ መሆኑን እንዳያውቅ የሚያደርገው ሲሆን፣ የውል መቋረጦች ሲከሰቱ የመንግስት ሊዝ ክፍያ በዕዳ እንዲታይ እና እንዲሁም ሌሎች እዳዎች በወቅቱ እንዳይታወቁ እና እንዳይሰበሰቡ ያደርጋል፡፡
98. አርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅን ተከራይቶ ከነበረው ባለሃብት ናሪን ኦርሜ ቴክስታይል ግሩፕ የተለያዩ እዳዎች ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ በብድር የተሰጠውን ዕዳ እና የኪራይ ክፍያ ባለመክፈሉ እንዲሁም ይህንን ድርጅት ተከራይቶ የነበረው ሚ/ር አቲላ የተባለ

ባለሀብት የተለያዩ ዕዳዎችን ባለመክፈሉ የኪራይ ውሉ እንዲቋረጥ መደረጉ፣ አዋሳ ጨርቃ ጨርቅን ተከራይቶ የነበረው ባለሃብት ናሪን ኦርሜ ቴክስታይል ግሩፕ የተለያዩ እዳዎችን ሳይከፍል ውል ማቋረጡ፣ ሬድ ስፔክልድ የተባለው የቀድሞ ሲሌ እርሻ ልማት ድርጅት ተከራይ የተለያዩ ዕዳዎች ያሉበት መሆኑ፣ እነዚህ እዳዎች በወቅቱ አለመከፈላቸው ድርጅቶች በገቡት ውል ስምምነትና በሥራ ዕቅዱ መሠረት ሥራቸውን ያላከናወኑ መሆኑን፣ በወቅቱ ክትትል አለመደረጉን እና የውል መቋረጥ ሲከሰት በተገባው ውለታ መሠረት ተፈጻሚ አለመሆኑን ያሳያል፡፡

99. ኤጀንሲው የፕራይቬታይዜሽን ትግበራ ያስከተለውን አጠቃላይ ውጤት ወጥነት ባለው ሁኔታ ባለመገምገሙ ለቀጣይ አፈፃፀም እርምት ሊወሰድባቸው የሚገቡ ጉዳዮች እንዳይለዩና አጠቃላይ የፕራይቬታይዜሽን ውጤት በጠራ መልኩ እንዳይታወቅ ያደርጋል፡፡

100. ኤጀንሲው በኪራይ በሰጣቸው የልማት ድርጅቶች ውስጥ በአደራ መልክ ተቀምጠው ያሉ የመንግስት ንብረቶች (ማሽኖች) በጥንቃቄ ባለመያዛቸው ሳር በቅሎባቸው፣ ፀሃይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው መቀመጣቸው እና በኪራይ በተያዙ ድርጅቶች ውስጥ ያሉ የመንግስት ንብረቶች (ማሽኖች) ለሶስተኛ ወገን ለኪራይ ተሰጥተው ለተከራዩ ድርጅት ገቢ እያስገኙ መሆናቸው የመንግስት ንብረት በተገቢው መንገድ ያልተያዘ መሆኑን ያሳያል፡፡

101. የልማት ድርጅቱን በጋራ ልማትና በኪራይ የሚይዘው ባለሀብት ለሰራተኞች የሚገባቸውን የጥንቃቄ መሳሪያዎች ባለማሟላቱ፣ የህብረት ስምምነቱ በሚያዘው መሰረት የሚገባቸውን ጥቅማ ጥቅም ማሟላት ባለመቻሉ፣ እንዲሁም ይህን እንዲያደርግ ኤጀንሲው የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ በሚያዘው መሰረት ባለሀብቱን ማስገደድ ባለመቻሉ የሰራተኛ ቅሬታ፣ መጉላላትና ተነሳሽነት ማጣት እንዲኖር እና የኢንዱስትሪ ሰላም እንዳይሰፍን ያደርጋል፡፡

102. ኤጀንሲው የመረጃ መረቡን ወቅታዊ ባለማድረጉና የቅርብ መረጃዎችን ባለማስቀመጡ ባለሀብቱ በቀላሉ ማግኘት የሚችለውን መረጃ ማግኘት እንዳይችል ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራምና አፈፃፀሙ በህዝቡ እንዳይታወቅ ያደርጋል፡፡

103. በአጠቃላይ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የልማት ድርጅቶችን በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ከግል ባለሃብቶች ጋር የማልማት አፈፃፀሙ በአንዳንድ ድርጅቶች ከቴክኖሎጂ ሽግግር እና ከኤክስፖርት አፈጻጸም አንፃር የታዩ መሻሻሎች ጥሩ ቢሆኑም፣ ነገር ግን በአንዳንድ ድርጅቶች የስራ ዕቅድ አፈፃፀም፣ ውል አፈጻጸም፣ የሪፖርት ልውውጥ፣ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት፣ የባለሃብትና ሰራተኛ ግንኙነት፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ የመንግስት ዕዳ ክፍያ አሰባበሰብ፣ የመንግስት ንብረት አያያዝ እና ፕራይቬታይዜሽኑ ያስከተለውን አጠቃላይ ውጤት መገምገምን በተመለከተ የተለያዩ ችግሮች ታይተዋል፡፡ ስለሆነም የታዩ ችግሮች ተስተካክለው እና በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት የተያዙ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የተቋቋሙበትን አላማ በብቃት፣ ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንዲፈፀሙ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች ቀጥለው ቀርበዋል፣

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሃሳቦች

ከላይ በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች እና መደምደሚያዎች መሰረት የሚከተሉት የማሻሻያ ሃሳቦች ተሰጥተዋል፡-

104. ኤጀንሲው በጋራ ልማት እና በኪራይ ድርጅቶችን ለመያዝ የሚሳተፉ ባለሀብቶችን ለመምረጥ የሚያቀርቡትን የሥራ እቅድ (ቢዝነስ ፕላን) ተፈጻሚነቱን ለማረጋገጥ ተጨባጭ በሆነ መልኩ በባለሙያ ግምገማ ሊደረግ እና ተፈጻሚነቱ የተሻለ የሚሆነውን የሥራ ዕቅድ መምረጥ ይገባል፡፡
105. በእርሻ ልማቶቹም ሆነ በሌሎች በኪራይ በተያዙ የልማት ድርጅቶች የስጋት መጠቆሚያ መስፈርቶችን አስቀድሞ በማዘጋጀት (በመጠቆም) ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን የመለየትና የመፍትሄ ሃሳቦችን በውሉ ላይ በማስቀመጥ የሚፈጠር የሥራ ዕቅድ አፈፃፀም መዘግየትን ለማስቀረት መጣር ይገባል፡፡
106. ኤጀንሲው በጋራ ልማትና በኪራይ ለሚሰጣቸው የልማት ድርጅቶች ባለሃብቶች በሥራ እቅዳቸው ውስጥ የአካባቢ ጥበቃን በማያሻማና ለመፈፀም አስገዳጅ በሚሆን መልኩ አስገብተው እንዲተገብሩት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም የልማት ድርጅቶች በአከባቢውና በመሬት ላይ የሚያደርሱት አሉታዊ ተጽዕኖ ሊገመገምና በሥራ ዕቅድ ላይ የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች ሊካተቱ ይገባል፡፡
107. ኤጀንሲው በጋራ ልማትም ሆነ በኪራይ ለግል ባለሀብቶች ለሰጣቸው የልማት ድርጅቶች የሥራ ዕቅድ ተፈፃሚነት የዘረጋውን የክትትል እና የመስክ ጉብኝት አሰራር ስርዓት ወጥ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
108. የተከራይ ድርጅት የቦርድ ጽ/ቤት በየሶስት ወሩ በኪራይ ስለተያዘው ድርጅት ስራ አፈፃፀም ከድርጅቶቹ ሰብስቦና አጠናቅሮ ለኤጀንሲው ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡
109. በጋራ ልማት ኢንቨስትመንትና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች የትርፍና ኪሳራ ሂሳብ ሪፖርት (Income statemenet) እና የሀብት እና እዳ ሂሳብ መግለጫ (Balance sheet) ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ሊያዘጋጁና ፈቃድ ባለው የኦዲት ተቋም ኦዲት ሊያስደርጉ ይገባል፡፡
110. የልማት ድርጅቶቹ በገቡት ውለታ መሰረት የኪራይ ክፍያና የመንግስትን የትርፍ ድርሻን (dividend) ክፍያን በውል ስምምነቱ መሠረት ሊከፍሉ ይገባል፡፡ እንዲሁም ኤጀንሲው በውል ዝግጅት ወቅት የክፍያ ዘመን መጠናቀቂያን በተመለከተ የሚታዩ ጉድለቶችን ለመጥቀስ የእፎይታ ጊዜ ክፍያን ግልፅ በሆነ መንገድ ሊያስቀምጡ ይገባል፡፡
111. ኤጀንሲው በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ከግል ባለሀብቱ ጋር የሚያስተዳድራቸው ድርጅቶች ስር ያለው የኃላፊነትና የተጠያቂነት ስርዓት በግልጽ መቀመጥ፣ እንዲሁም ከባለሀብቱ ጋር የተገባው ውል ቢቋረጥ አፈጻጸሙ በስምምነት ሰነዱ መሰረት መሆን አለበት፡፡

112. የውጭ ባለሀብቶች በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ስለያዙዋቸው የመንግስት የልማት ድርጅቶች የስራ አፈጻጸም እና ያስገኙትን ውጤት ከሥራ ዕቅዱ ጋር በተመሳከረ ሁኔታ በግልጽና በወቅቱ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡
113. የልማት ድርጅቶች በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ለግል ባለሀብቶች ከተሰጡ በኋላ ፕራይቬታይዜሽኑ ያስከተለውን አጠቃላይ ውጤት ኤጀንሲው በተወሰነ የጊዜ ገደብ መገምገም ይገባዋል፡፡
114. ጥቅም ላይ የማይውሉ ማሽኖች እና መለዋወጫዎች በደንቡ መሠረት ሊወገዱ እና በኪራይ ለሶስተኛ ወገን የተሰጡ የመንግስት ንብረቶች አሠራር ሊታረም ይገባል፡፡
115. በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ መሰረት በድርጅቱ የሥራ ቦታ የደህንነት እና የጥንቃቄ መሳሪያዎች መሟላታቸውን፣ በሰራተኛው ጤናና ህይወት ላይ ያሉ አሉታዊ ሁኔታዎች መወገዳቸውን ኤጀንሲው ሊከታተል ይገባል፡፡
116. በጡረታ ወይም በግል ምክንያት ሥራቸውን መልቀቅ ለሚፈልጉ ሰራተኞች የሥራ ዕቅዱንና ውሉን መሰረት ባደረገ መልኩ ጥቅማ ጥቅማቸውን በአግባቡ ማግኘታቸውን ኤጀንሲው ሊከታተል ይገባል፡፡
117. ባለሀብቱ ከሰራተኛ ማህበራት ጋር ያለው ግንኙነት የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ በሚያዘው መሰረት ሊሆን፣ ገገር የሆነ የህብረት ስምምነት ሊዘጋጅ እና የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ወደ ክስ ከማምራታቸው በፊት ሊፈታ ይገባል፡፡
118. ኤጀንሲው የመረጃ መረቡን ሙሉ መልዕክትን ሊሰጥ በሚችል እና ወቅታዊ በሆነ መልኩ ሊያደራጅ ይገባል፡፡

በመጨረሻም የኤጀንሲውና በናሙና የተመረጡ የልማት ድርጅቶች ኃላፊዎችና ሰራተኞች በኦዲቱ ወቅት የሚፈለጉ መረጃዎችን እና ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን በማቅረብ እንዲሁም ለኦዲቱ ለቀረቡ ቃለ መጠይቆች በወቅቱ መልስ በመስጠት ለተደረገልን ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1

የፐ/መ/ል/ድ/ተ ኤጀንሲ ድርጅታዊ መዋቅር



የፕራይቬታይዜሽን ዝግጅትና አፈጻጸም የሥራ ፍሰት — አባሪ 2



የድህረ ፕራይቬታይዜሽን ክትትልና ድጋፍ የሥራ ፍሰት



የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ አባሪ 3

ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፡- የፕራይቬታይዜሽን እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣ ኤጀንሲ

የኦዲት ጭብጥ /Issues/	የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/
1. በኪራይ እና በጋራልማት ወደ ግል ባለሃብቶች የሚተላለፉ የልማት ድርጅቶች የሚመረጡበት መስፈርት የተዘጋጀላቸው እና ተፈጻሚ መሆኑን፣ ኤጀንሲው ባለሃብቶችን ግልጽነት በተሞላበት እና ደንብ እና መመሪያን በጠበቀ መሠረት የሚመርጥ መሆኑን ማጣራት፣	1. ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ለሚዛወሩት የቅደም ተከተል የመምርጫ መስፈርት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
	2. ኤጀንሲው የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ከግል ባለሃብቶች ጋር በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ለመስጠት የተቀመጠ ግልጽ የመምረጫ እና የማወዳደሪያ መስፈርት ሊኖረው ይገባል፡፡
	3. የልማት ድርጅቶችን በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ለማልማት የሚወጣው ጨረታ ግልፅ እና ደንብና መመሪያን የተከተለ መሆን አለበት፡፡
	4. ለመጫረት የሚቀርቡ ድርጅቶች የሥራ ዕቅድ (business Plan) ግምገማን ግልጽና መመሪያን በተከተለ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡
	5. ኤጀንሲው ባለሀብቱን በሚመርጥበት ወቅት ለአገር የውጭ ምንዛሪ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂን ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡ እና የአገር ውስጥ ጥሬ እቃን የሚጠቀሙ ባለሃብቶች ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
	6. የልማት ድርጅቱን በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ላሸነፉ ባለሃብቶች ግልጽ በሆነ እና በተሟላ መልኩ መዝገብ ላይ በሠፈረ ሁኔታ ርክክብ መከናወን ይኖርበታል፡፡
	7. በአከራይና ተከራይ ወገኖች መካከል የሚጠበቀው ተግባርና ሀላፊነት በግልጽ በኮንትራት ውሉ በፅሁፍ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡
	8. በኪራይ ለተያዘው የልማት ድርጅት በውል ስምምነት ውስጥ የስጋት መጠቆሚያ መስፈርቶች (Periodic Risk Assessment) ሊኖሩ ይገባል፡፡

	9. አንድን ድርጅት በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ለመያዝ የዋጋ ትመናው ሲካሄድ በባለሙያ በታገዘ እና ወቅታዊ በሆነ መልኩ እንዲሁም ባለሀብቱ እንዲኖረው የሚፈለገው ድርሻና የመዋጮ መጠን በግልጽ ሊቀመጥ ይገባል፡፡
	10. ኤጀንሲው በኪራይ የተያዘውን የልማት ድርጅት ለመከታተል እንዲቻል የተከራይ ድርጅት ቦርድ ጽ/ቤት ማቋቋም አለበት፡፡
	11. ባለሃብቱ በሚያቀርበው የሥራ ዕቅድ ላይ የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ እቅድ እንዲኖረው የሚያስገድድ የአሰራር ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡
	12. የልማት ድርጅቱን የሚከራይ ባለሀብት ሊከራይ በሚሰማራበት የሥራ ዘርፍ ቢያንስ ለሶስት አመት ልምድ ያለው መሆን አለበት::
	13. በጋራ ልማት ኢንቨስትመንትና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶችን በተመለከተ በአሰሪና ሰራተኛው መካከል ያለው ግንኙነት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ መሰረት በጽሁፍና ግልጽ በሆነ መንገድ መቀመጥና ተፈፃሚ መሆን አለበት፡፡
2. በኪራይ እና በጋራ ልማት የተያዙ የልማት ድርጅቶችን የሥራ አፈጻጸም (ምርታማነትነ እና አገልግሎት አሰጣጥ) በኮንትራት ውሉ እና በሥራ እቅዱ(Business plan) መሠረት መሆኑን ክትትል የሚደረግ መሆኑን፣ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን እና በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ እየተፈጸመ መሆኑን ማጣራት፣	
	13. የልማት ድርጅቶች በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ወደ ግል ከተዛወሩ በኋላ በስራ እቅዱ (Business Plan) መሠረት ባለሀብቶች ሥራዎችን እየሰሩ ስለመሆኑ ወጥ የሆነ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	14. በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ለተያዙ የልማት ድርጅቶች በመስክ በመገኘት የክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ

2.1 በኪራይ እና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት የሚተዳደሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሥራ አፈፃፀምና ውጤት በታቀደለት መሰረት እየተከናወነ መሆኑን መገምገም፣	ይገባል፡፡
	15. የተከራይ ድርጅት የቦርድ ጽ/ቤት በየሶስት (3) ወሩ ስለስራው ሂደት ለኤጀንሲው ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡
	16. በጋራ ልማት ኢንቨስትመንትና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች የትርፍና ኪሳራ የሂሳብ ሪፖርት (Income statemenet)እና የሃብት እና እዳ መግለጫ (balance sheet) ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ሊቀርብና ፈቃድ ባለው የኦዲት ተቋም ኦዲት ሊደረግ ይገባል፡፡
	17. የልማት ድርጅቱ በገባው ውለታ መሰረት በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ለተያዙ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የኪራይ ክፍያና የመንግስትን የትርፍ መዋጮ በወቅቱ ሊከፍል ይገባል፡፡
	18. የውጭ ባለሀብቶች በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ስለያዙዋቸው የመንግስት የልማት ድርጅቶች የስራ አፈጻጸም እና ያስገኙትን ውጤት በግልጽና በወቅቱ ሊያሳውቁ ይገባል፡፡
	19. በግል ባለሀብቶች የተያዙ የልማት ድርጅቶች በአከባቢውና በመሬት ላይ የሚያደርሱት አሉታዊ ተጽዕኖ ሊገመገምና በሥራ ዕቅድ ላይ የሚቀመጡ የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች መከናወናቸውን ኤጀንሲው ሊከታተልና ሊያስፈጽም ይገባል፡፡
	20. የቦርድ ፅ/ቤቱ ሲዋቀር ከልማት ድርጅቶቹ የሥራ ሁኔታ ጋር የሚቀራረብ ሙያ ባላቸው አካላት መሆኑን እንዲሁም የቦርዱ ወጥ የሆነ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
	21. የልማት ድርጅቶች በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ለግል ባለሀብቶች ከተሰጡ በኋላ ፕራይቨታይዜሽኑ ያስከተለውን አጠቃላይ ውጤት ኤጀንሲው በተወሰነ የጊዜ ገደብ መገምገም አለበት፡፡
2.2 በኪራይ እና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት የተያዙ የመንግስት የልማት ድርጅቶች	22. ኤጀንሲው ለግል ባለሀብቶች በጋራ ልማት እና በኪራይ የሚያስተላልፋቸውን የልማት ድርጅቶች ንብረት የእርጅና ዋጋ (Depreciation cost) ትመና በባለሙያ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

ንብረት አጠባበቅና አያያዝ በብቃትና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መልኩ መሆኑን መገምገም፣	23. የልማት ድርጅት ወደ ግል ባለሀብት በኪራይ ሲዘዋወር በድርጅቱ ውስጥ ያለ ንብረት ተቆጥሮና ተመዝግቦ ሊተላለፍ ይገባል፡፡ 24. ባለሀብቱ በሥራ ዕቅዱ ላይ ያቀረባቸው የድርጅቱ ንብረቶችና አሰራሮች የልማት ድረጅቱን ከመረከቡ በፊት መገምገምና መመሳከር አለባቸው፡፡ 25. የመንግስት የልማት ድርጅት በኪራይ ወደ ግል ከተዛወረና ርክክብ ከተፈፀመ በኋላ በዋጋ ትመናው ወቅት ያልተካተቱ ንብረቶች ሊለዩ ይገባል፡፡ 26. ኤጀንሲው ወቅታዊ የሆነና የተደራጀ ለንብረት ትመና የሚያገለግል መረጃ ማዘጋጀት አለበት፡፡ 27. ለኪራይ እንዲውል የተመረጠ ድርጅት ሁሉ ንብረቶቹ ለኪራይ አገልግሎት ከመዋላቸው በፊት የድርጅቶች የንብረት ዋጋ በባለሙያ በትመና መታወቅ አለበት፡፡
2.3 የመንግስት የልማት ድርጅቶች በኪራይ ወይም በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት በሚዛወሩበት ወቅት የድርጅቱ ነባር ሰራተኞች አያያዝን መገምገም፣	28. በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ መሰረት በድርጅቱ የሥራ ቦታ የደህንነት እና የጥንቃቄ መሳሪያዎች ሊሟሉና በሰራተኛው ጤናና ህይወት ላይ ያሉ አሉታዊ ሁኔታዎች ሊወገዱ ይገባል፡፡ 29. በጡረታ ወይም በግል ምክንያት ሥራቸውን መልቀቅ ለሚፈልጉ ሰራተኞች የሥራን ዕቅዱንና ውሉን መሰረት ባደረገ መልኩ ጥቅማ ጥቅማቸውን በአግባቡ በደንቡ መሠረት ማግኘት አለባቸው፡፡ 30. አንድ የመንግስት የልማት ድርጅት ወደ ግል ባለሀብት ከተዛወረ በኋላ ነባር ሰራተኞች የጡረታና ሌሎች ጥቅማ ጥቅማቸው ሳይነካ በስራው እንዲቀጥሉ ማድረግና ባለሀብቱ ከሠራተኛ ማህበራት ጋር የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ በሚያዘው መሰረት የስራ ግንኙነት እንዲኖረው መመቻቸት አለበት፡፡
2.4 ኤጀንሲው በጋራ ልማት እና በኪራይ የተያዙ የልማት ድርጅቶች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሠራር መዘርጋቱንና ውጤታማ በሆነ	31. ኤጀንሲው የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና ህብረተሰቡ ወቅታዊ መረጃዎችን እንዲያገኙ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ 32. ኤጀንሲው የአገር ውስጥ ባለሃብቶች በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት እንዲሳተፉ ማበረታታት አለበት፡፡ 33. በልማት ድርጅቶች መካከል ሊኖር የሚገባውን ቅንጅታዊ አሰራር ሊያግዝ የሚችል መመሪያ ሊኖር ይገባል፡፡

መልኩ መከናወኑን ማረጋገጥ፣	34. ኤጀንሲው በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት በተያዙ የልማት ድርጅቶች መካከል ቅንጅታዊ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የአሰራር ሥራዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	35. ኤጀንሲው ከግል ባለሀብቱ ጋር በጋራ ልማት ኢንቨስትመንትና በኪራይ ሊያለማ ያሰባቸውን የልማት ድርጅቶች ሊለይና ሙሉ መረጃን በሚሰጡ መልኩ ማዕከላዊ በሆነ የኤጀንሲው የመረጃ መረብ ላይ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡
	36. የልማት ድርጅቶች በኪራይና በጋራ ልማት ኢንቨስትመንት ለግል ባለሀብቶች ከተሰጡ በኋላ ፕራይቬታይዜሽኑ ያስከተለውን አጠቃላይ ውጤት ኤጀንሲው በተወሰነ የጊዜ ገደብ መገምገም አለበት፡፡